# የቀዳማይ ልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት በኢትዮጵያ

## ብሔራዊ ፖሊሲ ማዕቀፍ

## 2005



## ራዕይ

ሁሉም ሕፃናት ጤናማ የሕይወት ጅማሬ የማግኘት፣ደህንነታቸው በተጠበቀ ሁኔታ የማደግ፣ ተንከባካቢና አነቃቂ አካባቢ የማግኘትና እምቅ ችሎታቸውን በተሟላ ሁኔታ የመዳበር መብታቸው ተረጋግጦ ማየት ነው።

የትምህርት ሚኒስቴር | የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር | የሴቶች፣ የሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር

# መልዕክት

የኢትዮጵያ መንግሥት የቀዳማይ ልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት ትኩረት ማግኘት ያለበትና ብዙ ሥራ ሊሠራበት የሚገባ ወሳኝ የዕድገት ወቅት መሆኑን ይረዳል። በዚህ የዕድገት ዘመን የተመጣጠነ ምግብ፣ የጤና እንክብካቤና ትምህርት ለሕፃናት አለማቅረብ ሕፃናትን ምርታማ ዜጋ እንዳይሆኑ ከማድረጉም በተጨማሪ የተሻለ ሕይወትን የመምራት ዕድላቸውን ያሰናክላል፤ ለማህበረሰቡ ሊያበረክቱ የሚችሉትን አስተዋጽዖም ያቀጭጫል።

የቀዳማይ የልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት ከጽንስ እስከ ሰባት ዓመት ዕድሜ ክልል ለሚገኙ ሕፃናትና ወላጆቻቸው ወይም ተንከባካቢዎቻቸው የሚሰጡ አገልግሎቶችን የሚያመላክት ሁሉን አቀፍ ፖሊሲና ፕሮግራምን ያካተተ ነው።

ይህ የፖሊሲ ማዕቀፍ የምክክር ሂደት ውጤት ሲሆን፣ ሁሉን አቀፍ፣ ሊተገበር የሚችልና አዋጭ የሆነ የቀዳማይ ልጅነትን እንክብባኬና ትምህርት እንዲኖር መሠረት ይጥላል። የዚህ ፖሊሲ መተግበር የሀገራችን ሕፃናት የተሻለና ጤናማ የሕይወት ጅማሬ እንዲኖራቸው አንድ እርምጃ ወደፊት ለመራመድ የሚያስችል ሲሆን፣ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ኃላፊነት የሚሰማቸውና ምርታማ ዜጋ እንዲሆኑ የሚያግዝ አካባቢና ሁኔታን ይፈጥራል።

የነባራዊ ሁኔታዎች ትንተና እንደሚያሳየው አሁን በቀዳማይ የልጅነት ዘመን ያለው የአመጋገብ፣ የጤና፣ የእንክብካቤና ትምህርት አገልገሎት ደካማ መሆኑን ነው። በመሆኑም በአመጋገብ፣ በጤና አያያዝ፣በሕፃናት መብት፣ በማነቃቃትና በትምህርት አሰጣጥ በኩል የሚደረጉ ማሻሻያዎች ግልጽ የሆኑ ማህበራዊ ጥቅሞች ያስገኛሉ። የቀዳማይ ልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት(ቀልዘእት) ውጤታማነት የሚወሰነው በትምህርት፣ በጤናና በሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ሠራተኞች/ባለሙያዎች መካከል በየደረጃው በሚኖረው ትብብር ነው።

ይህ የፖሊሲ ማዕቀፍ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት በቀዳማይ ልጅነት ዘመን መሰጠት ያለባቸውን አገልግሎቶች በመስጠት ረገድ የሚኖራቸውን ሚና በግልጽ ያስቀምጣል። የወላጆችን፣ የማህበረሰቡን፣ የመንግሥት የልማት አጋሮችን እንዲሁም የሌሎች ባለድርሻ አካላትን ኃላፊነት በዝርዝር ይገለፃል። በተጨማሪም ይህንን ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ ይረዳ ዘንድ ስትራቴጂያዊ የአተገባበር ዕቅድና መመሪያ ሰነዶች ራሳቸውን ችለው ተዘጋጅተዋል።

የእኛ ምኞትና ፍላጐት ፖሊሲውን በብቃትና በጥራት ተተግብሮ ለሁሉም ሕፃናት ተደራሽነት ያለው ፍትሐዊ የቀዳማይ የልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት አስተዳደር በሀገሪቱ እንዲሰርጽ ማድረግ ነው። ይህም የለጋ ሕፃናት እንክብካቤና ትምህርት በሀገራችን የልማት አጀንዳ ውስጥ ቅድሚያ እንዲያገኝ ይረዳል።

ፋአድ ኢብራሂም

የትምህርት ሚኒስትር ዴኤታ

# ማውጫ


ምኅፃረ ቃላት iii
መቅድም vi
1. መግቢያ 1
1.1. የሕዝብ ብዛትና የሕፃናት ሁኔታ በኢትዮጵያ 1
1.2. ኢኮኖሚ 1
1.3. የቀዳማይ ልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት 2
2. የነባራዊ ሁኔታ ትንታኔ 3
2.1. የሕፃናት አስተዳደግ ባህሪያትና ማህበራዊ ገጽታው 3
2.2. ጤናና ምግብ 3
2.3. ቀዳሚ ማነቃቂያና ትምህርት 7
2.4. ለቀልዘእት እየተሰጡ ያሉ ድጋፎችና የአገልግሎት አሰጣጥ ዘዴዎች 8
3. የአጠቃላይ ቀልዘእት ፖሊሲ ማዕቀፍ አስፈላጊነት 9
3.1. የቀልዘእት ፖሊሲ ማዕቀፍ አስፈላጊነት 9
3.2. የፖሊሲ አግባብ 10
3.3. የቀዳማይ ልጅነት ዓመታት ዕድገት ጠቀሜታ 10
3.4. በቀዳማይ ልጅነት ዓመታት ላይ የሚደረግ የመዋዕለ ንዋይ ፍሰት ጠቀሜታ 11
4. የቀልዘእት ፖሊሲ ማዕቀፍ 12
4.1. ራዕይ 12
4.2. ተልዕኮ 12
4.3. የቀልዘእት ፖሊሲ ማዕቀፍ መሪ መርሆዎች 12
4.4. ግቦችና ስትራቴጂያዊ ዓላማዎች 13
4.5. መዋቅራዊ አደረጃጀትና የተግባራት ትኩረት 13
5. ለቀልዘእት አገልግሎቶች አፈጻጸም የትብብር መዋቅር 18
6. በቀልዘእት አገልግሎት አቅርቦት የአጋሮች ሚናና ኃላፊነት 20
6.1. ወላጆችና ሌሎች የሕፃናት አሳዳጊዎች 20
6.2. ማህበረሰብ 20
6.3. የትምህርት ሚኒስቴር 21
6.4. የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር 21
6.5. የሴቶች፣የሕፃናትና የወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር(ሴሕወጉሚ) 21
6.6. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር 22
6.7. ዩኒቨርስቲዎችና የቀልዘእት የልህቀት ማዕከል 22
6.8. የሃይማኖት ተቋማት (የእምነት ድርጅቶች) 22
6.9. የሁለትዮሽና የብዙዮሽ የልማት አጋሮች 22
7. ማጠቃለያ 23
የአንዳንድ የእንግሊዝኛ ፅንሰ ሀሳብ ፍቺዎች 25

## ምኅፃረ ቃላት

| | |
|---|---|
| ቀልዘእት | ቀዳማይ የልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት |
| ክትቢ | ክልል ትምህርት ቢሮ |
| ወትጽቤ | ወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት |
| ክጤቢ | ክልል ጤና ቢሮ |
| ወጤጽቤ | ወረዳ ጤና ጽ/ቤት |
| ሴሕወጉሚ | ሴቶች፣የሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር |
| ክሴሕወጉቢ | ክልል ሴቶች ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ |
| ወሴሕወጉጽ | ቤወረዳ ሴቶች ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት |

# መቅድም

በሰው ልጅ የሕይወት ሂደት ውስጥ ቀዳማይ የልጅነት ዘመን ወሳኝነት ያለው፣ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባና ብዙ መዋዕለ ንዋይ የሚያስፈልገው ነው። በዚህ ደረጃ ለሕፃናት የተሻለ ምግብ፣የጤና እንክብካቤና ትምህርት መስጠት አለመቻል ሕፃናት ምርታማ ዜጋ የመሆን፣ የተሻለ ሕይወትን የመምራት መብታቸውንና ለማህበረሰብ ዕድገት የሚያበረክቱትን አስተዋፆኦ ይገታል። የቀዳማይ ልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት ከጽንስ እስከ 7 ዓመት ያለውን ዘመን አስመልክቶ ለሕፃናት፣ ለወላጆች/አሳዳጊዎችና ለተንከባካቢዎች መሰጠት ያለባቸውን አገልግሎቶች በሚመለከት ሁሉን አቀፍ ፖሊሲና ኘሮግራምን ይመለከታል።

የቀዳማይ ልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት በኢትዮጵያ በቂ ትኩረት ካልተሰጣቸው መስኮች መካከል አንዱ ሆኖ ቆይቷል። ለዚህም በ2001 ዓ.ም በቀዳማይ ልጅነት ትምህርት ቤት የተመዘገቡት ሕፃናት ብዛት 4.2% ብቻ መሆኑ በቂ ማስረጃ ነው።

ካለፉት ጥቂት አመታት ወዲህ በከተሞች አካባቢ የግል ባለሀብቶች በቀዳማይ የልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት ላይ መዋእለ ንዋያቸውን በማፍሰስ ላይ ናቸው። ይሁን እንጂ የዚህ እድል ተጠቃሚ የሚሆኑት ከተሻለ የኑሮ ደረጃ የሚመጡ ጥቂት ሕፃናት ብቻ ናቸው።

የዚህ የቀዳማይ ልጅነት እንክብካቤና ትምህርት የፖሊሲ ማዕቀፍ ዋና ዓላማም የቀዳማይ ልጅነት እንክብካቤና ትምህርት ላይ በቂ ትኩረት ባለመሠጠቱ አገልግሎቱን ሳያገኝ የቆየውን የማህበረሰቡን ፍላጐት ማሟላት ነው።

ፖሊሲው የተቀረፀው በመጀመሪያ በሀገሪቱ የቀዳማይ ልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት ያለበትን ሁኔታ ለማወቅ በተደረገው ሀገር አቀፍ ጥናታዊ ዳሰሳ ላይ ተመርኩዞ ነው።

ጥናቱን አስመልክቶ በተደረገው አውደ ጥናት ላይ በተላለፈው ውሳኔ መሠረት የቀዳማይ ልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት ግብረ-ኃይል እንዲቋቋም ተደረገ። ይህም ከትምህርት ሚኒስቴር፣ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ከሴቶች ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከዩኒሴፍ፣ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ከኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ፣ ከሕፃናት አድን ድርጅት ኢትዮጵያና ከመሠረታዊ ትምህርት ጥምረት/ኔትወርክ የተውጣጡ ተወካዮችን የያዘ ነው። ይህ ግብረኃይል የፖሊሲ ማዕቀፉን፤ ስትራቴጂያዊ የአተገባበር ዕቅድና መመሪያ ሰነዶችን አዘጋጅቶ ለከፍተኛ አመራር በማቅረብ እንዲፀድቁ አድርጓል። የሀገር ዓቀፍ የፖሊሲ ማዕቀፍ፣የስትራቴጂክ የትግበራ እቅድ እና መመሪያ በሀገሪቱ እንዲኖሩ መደረጉ የብዙ ሕፃናትን ሕይወት ሊለውጥ ይችላል ተብሎ ታምኖበታል።

# 1. መግቢያ

## 1.1 የሕዝብ ብዛትና የሕፃናት ሁኔታ በኢትዮጵያ

ኢትዮጵያ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መኖሪያ ሀገር ናት። የዚህ ማሳያ በሀገሪቱ ከ80 በላይ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች መገኘታቸው ነው። አብዛኛው የሀገሪቱ ሕዝብ በከፍታማ መልከዓ ምድር የሚኖር ነው። በአንድ ቦታ ላይ በቋሚነት ሰፍሮ የሚኖረው ሕዝብ መተዳደሪያው በአብዛኛው ግብርና ሲሆን፣ በዝቅተኛ ቦታ የሚኖሩ አርብቶ አደሮች ለከብቶቻቸው ግጦሽና ውሃ ፍለጋ ከቦታ ቦታ ይዘዋወራሉ። በሀገሪቱ ውስጥ ክርስትናና እስልምና ብዙ ተከታይ ያላቸው ሃይማኖቶች ናቸው።

ሕፃናት ከሕዝቡ ቁጥር ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ። በሀገሪቱ ካለው 80 ሚሊዮን ከሚገመት ሕዝብ ውስጥ 33 ሚሊዮን ወይም 55% የሚሆኑት ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናት ናቸው።[1] እንደሌሎች ታዳጊ ሀገሮች በኢትዮጵያም ሕፃናት አስፈላጊውን አገልግሎት የማግኘት ዕድላቸው አነስተኛ ነው። እንደ ትምህርትና ሥልጠና፣ ጤና፣ በቂና የተመጣጠነ ምግብና የመዝናኛ ቦታዎች የመሳሰሉት አገልግሎቶች የማግኘት ዕድላቸው ውስን ነው። ከዚህ በተጨማሪ ቁጥራቸው ቀላል የማይባል ሕፃናት ለተለያዩ ብዝበዛዎችና እንግልቶች የተጋለጡ በመሆናቸው ያላቸው እምቅ ችሎታ እንዲዳፈን ሆኗል።

## 1.2 ኢኮኖሚ

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በአብዛኛው ግብርና ላይ የተመሠረተ ነው። የግብርናው ዘርፍ ከ80% በላይ ለሚሆነው የሀገሪቱ ሕዝብ መተዳደሪያ ሲሆን ከአጠቃላይ የአገሪቱ ምርት ውስጥ 47% ብሔራዊ ገቢና 90% የሚሆነው የሀገሪቱ የወጪ ንግድ የሚገኘው ከዚሁ ዘርፍ ነው። ኢትዮጵያ በዓለም ላይ ካሉ ድሃና ታዳጊ ሀገራት አንዷ ስትሆን የዓለም ባንክ በ2000 ዓ.ም ይፋ ባደረገው ሪፖርት መሠረት የአንድ ሰው የነፍስ ወከፍ ገቢ 280 ዶላር ብቻ ነው። ሀገሪቱ እ.ኤ.አ ከ1974-1992 በደርግ ዘመነ መንግሥት የዕዝ ኢኮኖሚ ሥርዓት የምትከተል የነበረ ሲሆን ከዚህ መንግሥት ውድቀት በኋላ ወደ ነፃ ገበያ የኢኮኖሚ ሥርዓት ተሸጋግራለች። ምንም እንኳን ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ ሀገሪቱ እምቅ ሀብቷን በመጠቀም መጠነኛ ዕድገት ብታሳይም ዕድገቱን ቀጣይ ለማድረግ ከባድ ተግዳሮቶች ይጠብቋታል።

1 ምንጭ ፣አመታዊ የሕዝብ ቆጠራ ሪፖርት 1999 ዓ.ም.

## 1.3 የቀዳሚይ ልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት

መንግሥት የቀዳሚይ ልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርትን ለሁሉም ሕፃናት ማዳረስ እና የምዕተ ዓመትን የልማት ግቦች ማሳካት ያለውን ጠቀሜታ በሚገባ ተረድቷል። ይህ ሰነድ ዋናና አጠቃላይ የፖሊሲ ማዕቀፉን የያዘ ሲሆን በውስጡም ከፅንስ እስከ 7 ዓመት ላሉ ሕፃናት ቀልዘእትን በተመለከተ የየዘርፉን ፖሊሲዎች አካትቶ የያዘ ነው። ይህ የፖሊሲ ማዕቀፍ ለጨቅላና ለጋ ሕፃናት አገልግሎት ለመስጠት ለሚሰማሩ ዘርፎች እንደ ዋና መነሻና ማጣቀሻ በመሆን ያገለግላል። በተጨማሪም ይህ የፖሊሲ ማዕቀፍ ለሌሎች በተለይም ለጤና፣ሥነ-ምግብ፣ትምህርት፣ሕፃናትና የማህበረሰብ አገልግሎት ዘርፍ ፖሊሲዎች እንደ መንደርደሪያ በማገልገል ራሳቸውን የሚያጠናክሩበት፣የሚፈትሹበትና የሚያሳድጉበት ይሆናል። እነዚህ የየዘርፉ ፖሊሲዎች የጥራት ደረጃዎችንና ዝርዝር መመሪያዎችን በማውጣት ለሁሉም ሕፃናት በቀጣይ ሕይወታቸው ጥራቱንና ደረጃውን የጠበቀ ግልጋሎት እንዲኖር ለማስቻል ጠቀሜታ አላቸው። ሀገር አቀፍ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ፣ሀገር አቀፍ የጤና ፖሊሲ፣ሀገር አቀፍ የሥነ-ምግብ ስትራቴጂ ፖሊሲና የሕግ ማዕቀፍ ለሕፃናት መብት መረጋገጥ ግብአቶች ናቸው።

# 2. የነባራዊ ሁኔታ ትንታኔ

## 2.1 የሕፃናት አስተዳደግ ባህሪያትና ማህበራዊ ገጽታው

በኢትዮጵያ ለሕፃናት ተገቢ እንክብካቤና ትምህርት መስጠት በአመዛኙ ለቤተሰብና ለማህበረሰቡ የተተወ ነው። ማንኛውም የማህበረሰቡ አባል ሕፃናትን ከአደጋ መከላከልና በማህበረሰቡ ተቀባይነት የሌላቸው ጠባዮች ሲያሳዩ መገሰጽና ማስተካከልን እንደ አንድ የሥራ ድርሻ አድርጎ ሲቆጥረው ቆይቷል። ይሁን እንጂ ይህ መልካም ባህል አሁን አሁን በተለይም በከተሞች እየቀነሰ መጥቷል። በመሆኑም ሕፃናት ያልተገባ ባህርይ ሲያሳዩ፤ ለምሳሌ ሲሳደቡ፣ ድንጋይ ሲወራወሩ እና ሲደባደቡ አጠገባቸው ያሉ አዋቂዎች ምንም ቦታ ሳይሰጡት ይስተዋላሉ።

በአጠቃላይ የነባራዊ ሁኔታው ትንታኔ እንደሚያሳየው አብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ሕፃናት በአስቸጋሪ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ ያሉ እና ለተለያዩ ጥቃቶች የተጋለጡ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ አካላዊ ጥቃት ተጠቃሽ ነው። ይህ ክስተት ሕፃናት የተሻለ የሕይወት ጅማሮ እንዳይኖራቸው ያደርጋል። የሴት ልጅ ግርዛት፣እንጥል ማስቆረጥ፣የሕፃናት የጉልበት ብዝበዛ፣ ያልተስተካከለ የአመጋገብ ስርዓት፣ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እና የመሳሰሉት በሕፃናት ዕድገት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ወይም ጉዳት ያስከትላሉ። አብዛኛው ሕዝብ ያልተማረ በመሆኑ (61.5%)[2] ወላጆችም በሕፃናት እንክብካቤና ትምህርት ላይ የተሠሩ የምርምር ውጤቶችን የማወቅ ዕድላቸው ውስን ነው። ይህ ሁኔታ መኖሩ የወላጆችንና የሕፃናት አሳዳጊዎችን ትምህርት አስፈላጊነት ቀዳሚ ተግባር እንዲሆን አድርጎታል።

## 2.2 ጤናና ምግብ

### 2.2.1 የሕፃናት ሞት

የሕፃናት ሞት በኢትዮጵያ ከፍተኛ ነው። በ1997 ዓ.ም ከሥነ ሕዝብና ጤና ዳሰሳ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው ከ13 ሕፃናት ውስጥ አንዱ ዕድሜው አንድ ዓመት ከመሆኑ በፊት ይሞታል። መረጃው አክሎ እንደጠቆመው ከ8 ሕፃናት አንዱ አምስት ዓመት ሳይሞላው ይሞታል። ሃምሳ በመቶ (50%) የሚሆነው የሕፃናት ሞት የሚከሰተው በተወለዱ በመጀመሪያ ወር ውስጥ ነው። ዘጠና አምስት በመቶ (95%) ለሚሆነው ከአምስት ዓመት በታች ለሚከሰተው ሞት የመነሻ ምክንያቶች በአብዛኛው የሳንባ ምች፣ በአራስነት ሰዓት የሚከሰት ችግር፣ ወባ፣ ተቅማጥና ኩፍኝ ናቸው። ከግማሽ በላይ በሚሆኑት የሕፃናት ሞት ውስጥ አጣዳፊ የምግብ እጥረት በሽታ እንዳለባቸው ይስተዋላል። ባለፉት 15 ዓመታት በዚህ በኩል አበረታች ለውጥ ታይቷል። ለዚህም በማስረጃነት የሚከተሉትን አኃዛዊ ለውጦች ማየት ይቻላል። የጨቅላ ሕፃናትን ሞት በሚመለከት ከ1000 ሕፃናት ውስጥ የሚሞተው ቁጥር 95 የነበረ ሲሆን ይህ አኃዝ በ19% በመቀነስ ወደ 75.2 ዝቅ ብሏል። በሌላ በኩልም ዕድሜያቸው ከአምስት ዓመት በታች ከሆኑት 1000 ሕፃናት ውስጥ 166 ይሞት የነበረው በ25% በመቀነስ ወደ 123 ዝቅ ብሏል።

2 ምንጭ 3፡ በኢትዮጵያ የጎልማሶች የትምህርት ሁኔታ (ዓለም ባንክ 2000 ዓ.ም)

በአራስነት/የጨቅላ ሕፃናት ሞት እና ከአራስነት በኋላ/ዕድሜያቸው አንድ ዓመት ያልሞላ ሕፃናት ሞት በቅደም ተከተላቸው መሠረት በ15% እና በ22% ቀንሷል። የሕፃናት ሞት ከገጠር ይልቅ በከተማ ይቀንሳል።

የእናቶች የትምህርት ደረጃ ከሕፃናት ሞት ጋር በእጅጉ ይቆራኛል። ለምሳሌ፣ ዕድሜያቸው ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ ካልተማሩ ወላጆች የተወለዱ ሕፃናት የሞት ቁጥር ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርትና በላይ ከተማሩ ወላጆች የተወለዱ ሕፃናት ጋር ሲነፃፀር በሁለት እጅ ይበልጣል።

የሀገሪቱ የጤና ፖሊሲ በዋናነት ትኩረት ከሚያደርግባቸው ጉዳዮች መካከል የቤተሰብን የጤና ፍላጐት ማሟላት አንዱ ነው። የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በ1996 ዓ.ም ሀገር አቀፍ የሕፃናት አድን ስትራቴጂ አዘጋጅቷል። የስትራቴጂው ዋና ዓላማ የሕፃናትን ሞት ሊያስከትሉ የሚችሉ መንስኤዎች ላይ ትኩረት በማድረግ ፈጣን ለውጥ ማምጣት ነው። በእርግጥ የሕፃናት ሞትን የሚያባብሱ ምክንያቶች ለምሳሌ የትምህርት እጦት፣ ሴቶች በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸው ቦታ ዝቅተኛ መሆን፣ በቂ ውሃና ምግብ አለማግኘት የመሳሰሉት በጤና ዘርፍ ብቻ ሊፈቱ የማይችሉ ችግሮች ናቸው። በመሆኑም የስትራቴጂው ተፈጻሚነት በሌሎች ሕፃናት ላይ ቀጥተኛ ተፅዕኖ ሊያመጡ የሚችሉ ሥራዎች እና ዘርፎች ላይ የተሰማሩ አካላት ትብብር ይጠይቃል።

### 2.2.2 የእናቶች ጤና

ከ15-49 ዓመት የዕድሜ ክልል ከሚገኙ 100,000 እናቶች ውስጥ 670 የሚሆኑት ከወሊድ ጋር በተያያዙ ምክንያቶች ይሞታሉ። ከ10 እናቶች ውስጥ 7 የሚሆኑት የቅድመ ወሊድ ክትትል አያደርጉም። በኢትዮጵያ 94% ሕፃናት የሚወለዱት በቤት ውስጥ ነው። አምስት በመቶ የሚሆኑት በመንግስትና 1% የሚሆኑ ደግሞ በግል የጤና ተቋማት ውስጥ ይወለዳሉ። ጥናቶች እንደሚጠቁሙት በአብዛኛው እናቶች የሚወልዱት ቤት ውስጥ በዘመዶቻቸው እርዳታ ሲሆን 5% የሚሆኑት ግን ካለምንም እርዳታ ይወልዳሉ። በተጨማሪም እናቶች የሚያደርጉት የድኅረወሊድ ክትትል እጅግ ዝቅተኛ ነው።[3]

መንግሥት ከአጋሮቹ ጋር በመሆን የእናቶችንና የሕፃናትን ጤና ለማሻሻል በብሔራዊ ፖሊሲ ማለትም በጤና ኤክስቴንሽን ኘሮግራም በመታገዝ ከላይ የተጠቀሱትን የጤና ችግሮች በማስወገድ ላይ ይገኛል። ጤና የሚጠበቀው በራሱ በግለሰቡና በማህበረሰቡ መሆኑን በማመን የጤና ኤክስቴንሽን ኘሮግራሙ ማህበረሰቡ ጤንነቱን በሚመለከት ዕውቀትና መረጃን መሠረት ያደገ ውሳኔ እንዲወስን ለማስቻል ዕውቀቱንና ክህሎቱን ያሳድጋል። ይህን ዕቅድ ከግቡ ለማድረስ መንግሥት ከ30,000 በላይ የሚሆኑ ሴት የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችን ከ15,000 በላይ በሚሆኑ የጤና ኬላዎች አሰማርቷል። ይህ ማለት በአንድ ቀበሌ ቢያንስ ሁለት የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ተመድበዋል ማለት ነው። የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ከ16 የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆች ውስጥ የሕፃናት አመጋገብ፣ ዕድገት፣ ጤና እንዲሁም የሕፃናትና የእናቶች ሞት መከላከል ከሚያከናውኗቸው ሥራዎች ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

3 ምንጭ በኢትዮጵያ የሥነ-ሕዝብና የጤና ዳሰሳ፣1997 ዓ.ም

### 2.2.3 የሕፃናት አመጋገብ

በኢትዮጵያ ሕፃናት አሳሳቢ ለሆነ ላልተመጣጠነ አመጋገብ የተጋለጡ ናቸው። ለዚህ አስረጅ ተደርገው የሚወሰዱት የሚከተሉት ሁኔታዎች ናቸው። ከአምስት ዓመት በታች ካሉ ሁለት ሕፃናት አንዱ (47%) ላልተመጣጠነ አመጋገብ የተጋለጠ ነው። በ6 ወር ዕድሜ ላይ ከሚገኙ ሕፃናት 32% የሚሆኑት ብቻ የእናት ጡት ወተት ብቻ ይጠባሉ። ከበሽታ የሚከላከልላቸውንና በጠቃሚ ንጥረ ነገሮች የበለፀገውን የመጀመሪያ ወተት/እንገር ወይም ኮሎስትሮም (Colostrum) የሚያገኙት ከግማሽ በታች (45%) ናቸው። ተጨማሪ ምግቦች ወቅታቸውን ጠብቀው በትክክለኛው ዕድሜ ማለትም ከ 6 ወር በኋላ ለሕፃናት አይሰጡም። የአዮዲን (iodine) እጥረት ያለባቸው ሕፃናት 83% ሲሆኑ፣ ከነዚህ ውስጥም 39% የሚሆኑት በእንቅርት በሽታ የተያዙ ናቸው። ከ6 እስከ 59 ወራት እድሜ ካላቸው ሕፃናት ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በደም ማነስ በሽታ የተጠቁ ናቸው። ያልተመጣጠነ አመጋገብ በእናቶች ላይም ጎልቶ የሚታይ ሲሆን ከእነዚህ እናቶች የሚወለዱ ሕፃናት ከአመጋገብ ጋር በተያያዘ ምክንያት ለዘርፈ ብዙ ችግሮች ተጋላጭ ይሆናሉ። ምንም እንኳ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ በተወሰኑ የሀገሪቱ ክፍሎች አስቸጋሪ ቢሆንም በምርታማነት ላይ ያተኮረው የሴፍቲ ኔት ኘሮግራም እና ሌሎች የምግብ ዋስትና ማረጋገጫ ዘዴዎች እየተከናወኑ ናቸው። ሌሎች ያልተመጣጠነ አመጋገብን ከሚያመጡ ምክንያቶች መካከል በበቂ ሁኔታ የመንከባከብና የመመገብ ልምድ አለመኖር፣ የበሽታዎች/ኢንፌክሽን መከሰት፣ የንጽህና እጦት፣ የእናቶች ያልተመጣጠነ አመጋገብ፣ እናቶች ለልጆቻቸው የመመገቢያ ጊዜ ማጣት ተጠቃሽ ናቸው። ይህን ችግር ለማቃለል የኢትዮጵያ መንግሥት አጠቃላይ የብሔራዊ የሥርዓተ-ምግብ ስትራቴጂ በየካቲት ወር 2000 ዓ.ም ያፀደቀ ሲሆን ለአፈፀሙም ከልማት አጋሮቹ ጋር በመተባበር ላይ ይገኛል።[4]

### 2.2.4 የልደት ምዝገባ

በኢትዮጵያ የልደት ምዝገባ የሚከናወንበት ደረጃውን የጠበቀ ህጋዊና አስተዳደራዊ መዋቅር የለም። በከተማ አካባቢ የልደት የምሥክር ወረቀት የሚሰጥ ሲሆን በአብዛኛው የሚከናወነው የውልደት ምዝገባ ሳይኖር ነው። ከነባራዊ ሁኔታ ትንታኔ በተገኘው መረጃ መሠረት በኢትዮጵያ ውስጥ ከአምስት ዓመት በታች ካሉ ሕፃናት 7% ብቻ የልደት ምዝገባ ያከናውናሉ።[5] ከነዚህ ውስጥ በአብዛኛዎቹ (95%) የልደት የምስክር ወረቀት የላቸውም። ይሁን እንጂ ውልደትን ጨምሮ ወሳኝ ኩነቶችን ለመመዝገብ በወቅቱ በአቅም ግንባታ ሚኒስቴር የምርምር ኢንስቲትዩት የምዝገባ ሕግ ረቂቅ እንዲያዘጋጅ ኃላፊነት ተሰጥቶታል። በተመሳሳይም በፍትሕ ሚኒስቴር የሚመራ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ከተለያዩ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች በተውጣጡ ባለሙያዎች የተዋቀረ ኮሚቴ አለ። ኮሚቴው የተቋቋመበት ዋና ዓላማና ኃላፊነት የልደት ምዝገባን በተመለከተ ማዕቀፍ ማዘጋጀት ነው። አሁን በኢትዮጵያ የመሠረታዊ ኩነቶች ምዝገባ ሕግ ፀድቋል።

---

4 ምንጭ፣ በኢትዮጵያ የብሔራዊ የሥነ-ምግብ ዳሰሳ ጥናት (ዩኒሴፍ 1998-1999)

5 ምንጭ፣ በኢትዮጵያ የሥነ-ሕዝብና የጤና የአሰሳ ጥናት፣ 1997 ዓ.ም

### 2.2.5 ወላጆቻቸውን ያጡና ለችግር የተጋለጡ ሕፃናት

በ1995 ዓ.ም ወላጆቻቸውን ያጡ እና ለችግር የተጋጡ ሕፃናትን ሁኔታ በተመለከተ የተሰበሰበው መረጃ እንደሚያሳየው በኢትዮጵያ ውስጥ 5.4 ሚሊዮን ወይም 13% የሚሆኑ ሕፃናት ወላጅ ያጡ ናቸው።[6] ሁለቱን ወይም አንዱን ወላጆቻቸውን በኤች አይ ቪ/ ኤድስ ያጡ ሕፃናት ቁጥር 855,720 ይጠጋል። ይህ ቁጥር በተመሳሳይ ዓመት 4.4.% የኤች አይቪ የስርጭት መጠን ባለባት ኢትዮጵያ እንደሚጨምር ይጠበቃል። የእነዚህ ወላጆቻቸውን ያጡ ሕፃናት የችግር ተጋላጭነት እንደሚያመለክተው 42% የሚሆኑት ሴቶች ወይም እናቶች ብቻ የሚያሳድጓቸው ናቸው። ከአሥር እስከ አስራ ሁለት ዓመት ባለው የዕድሜ ክልል ውስጥ ወላጆቻቸውን ያጡ ሕፃናት የትምህርት ተሳትፎ ገፅታ እንደሚያሳየው ሁለቱን ወላጆቻቸውን ያጡት 26% ሲሆን አንዱን ያጡት ደግሞ 34% ነው። በብሔራዊ ደረጃ ወላጆቻቸውን ስላጡ ሕፃናት ተጨማሪ የሕይወት ገጽታዎችን የሚያሳይ መረጃ የለም።[7]

### 2.2.6 የሕፃናት መብት ጥበቃና እንክብካቤ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ፖሊሲና የሕግ ማዕቀፍ እንደሚያመለክተው የሕፃናት መብት ጥበቃ እንክብካቤ አጠቃላይ ደህንነትና ትምህርት መሠረቱን እንዲጥልና ወደፊት እንዲራመድ መንግሥት ግልፅ የሆነ ቁርጠኝነት አለው። የሕፃናትን መብት በተመለከተ እ.ኤ.አ. በ1995ቱ የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 36 ላይ ተቀምጧል። በዚህ ህገ-መንግሥትና ሀገሪቱ ተቀብላ ባፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ላይ ኢትዮጵያ የሕፃናትን መብት ለማክበርና ትምህርትን ለሁሉም ሕፃናት ለማዳረስ ቃል ገብታለች።

ይህ የሚያመለክተው ሀገሪቱ የቀልዘእትን ዕድገት የማገዝ ግዴታ እንዳለባት ሲሆን፣ የዚህም የፖሊሲ ማዕቀፍ መውጣት የኢትዮጵያ ሕፃናት መብት እንዲከበር ማድረግን ያጠቃልላል።

ሕፃናትን ከጥቃት መጠበቅን በሚመለከት የአፍሪካ የሕፃናት ፖሊሲ ፎረም በ1999 ዓ.ም በሀገሪቱ የፖሊሲ መመሪያዎች ቢኖሩም አፈፃፀማቸው ግን የሚጠበቀውን ያህል አይደለም በማለት ዘግቧል። በሀገሪቱ ባህላዊ ስነልቦናዊና አካላዊ ቅጣቶች የሕፃናትን ባህርይ ለመቅረጽ ትክክለኛ መንገዶች ተደርገው ይቆጠራሉ። ሕፃናትን መምታት የተለመደና የተዘወተረ የቅጣት ዓይነት ነው። ትምህርት ሚኒስቴርና የክልል ትምህርት ቢሮዎች ሕፃናት ላይ ማንኛውም ዓይነት ሥነ-ልቦናዊና አካላዊ ቅጣቶች እንዳይፈፀሙ መመሪያ አውጥተዋል። ይሁን እንጂ በአፈፃፀሙ ላይ በቂ ክትትል ባለመደረጉ አሁንም ድረስ በትምህርት ቤቶች ውስጥ ተማሪዎች የአካላዊና ሥነ-ልቦናዊ ቅጣቶች ሰለባ ናቸው። የፖሊሲውና የሕጉ አተገባበር ድክመት የሚያሳየው የሕፃናት መብትን ለመጠበቅና ከጥቃት ለመከላከል ብዙ መሠራት እንዳለበት ነው። ስለዚህ መንግሥትም በገባው ግዴታ መሠረት በአፈፃፀሙ ላይ ክትትል ማድረግ ይኖርበታል።

---

6 ምንጭ፣ በኢትዮጵያ ወላጆቻቸውን ስለአጡና ለጥቃት ስለተጋለጡ ሕፃናት፣1999

7 ምንጭ፣ የዓለም ሕፃናት ገጽ፣2001 ዓ.ም ኢትዮጵ 1999 ዓ.ም

### 2.2.7 የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ

በኢትዮጵያ አብዛኞቹ ሕፃናት በቤት ውስጥ ሥራ፣ በእረኝነት፣ ለታናናሽ እህቶቻቸውና ወንድሞቻቸው ሞግዚትነትና ለሌሎች የጉልበት ሥራዎች የተዳረጉ ናቸው። ከ5 እስከ 14 ዓመት እድሜ ካላቸው ሕፃናት ውስጥ 53% የሚሆኑት ለጉልበት ብዝበዛ የተጋለጡ ሲሆን ከ5 እስከ 11 ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ሕፃናት ቢያንስ በቀን ለአንድ ሰዓት በኢኮኖሚያዊ ተግባር ላይ ይሰማራሉ፤ ወይም በሳምንት ለ28 ሰዓታት በቤት ውስጥ ሥራ ይጠመዳሉ። ከ12 እስከ 14 ዓመት የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ሕፃናት በሳምንት ቢያንስ ለ14 ሰዓታት በኢኮኖሚ ተግባር ላይ ወይም ቢያንስ ለ28 ሰዓታት በቤት ውስጥ ሥራ ይሰማራሉ8።

## 2.3 ቀዳሚ ማነቂቂያና ትምህርት

በኢትዮጵያ በቤት ውስጥ ብዙ ሰው ከጨቅላና ለጋ ሕፃናት ጋር መጫወትን ይወዳል። ይህም በእንቆቅልሽ በጥያቄ እና መልስ መልክ ይቀርባል። በዚህ ሂደት ውስጥ ጎልማሶች ሕፃናትን በትዕግስት ያዳምጣሉ። ወላጆችና ሞግዚቶች በተለምዶ የሥነ-ልቦናና ማህበራዊ ማነቃቃትን ለሕፃናት ያደርጋሉ። በገጠር እናቶች የትም ሲሄዱ ሕፃናትን አዝለው ይሄዳሉ። ይህም የሕፃናትን አካላዊ፣ሥነልቦናዊ እና ማህበራዊ ፍላጐቶች ከሚሟላት ጋር የተያያዘ ነው። ሆኖም ግን ድርጊቱ በግንዛቤ ላይ ተመስርቶ የሚከናወን አይደለም። በገጠር ሕፃናት በለጋ ዕድሜያቸው የተለያዩ ኃላፊነቶች ይሰጧቸዋል። ከነዚህ ኃላፊነቶች መካከል ጥጃ መጠበቅ፣ ለከብት ሳር ማቅረብና የመሳሰሉት ለሕፃናት ቀዳሚ ማነቃቃት ተጠቃሽ ናቸው።

በቀደማይ የልጅነት ዘመን የሚያስተምሩ መምህራንም በብዛት የሚሰማሩበት ተግባር የሕፃናትን የማንበብ፣የመጻፍና ቀላል የሒሳብ ቀመሮችን ማሳወቅ ላይ ነው። የማነቃቃት፣ በጨዋታ መልክ ሕፃናትን ማስተማር በዚህ የማስተማር ዘዴ ውስጥ በበቂ ደረጃ ተካቷል ማለት ያዳግታል። ይህ የሚያመለክተው ሕፃናት ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲያሳድጉ፣ የቋንቋና የማህበራዊ ክህሎታቸውን እንዲያጎለብቱ፣ በአጠቃላይ መነቃቃት እና አዳዲስ አካባቢዎችን በቀላሉ እንዲለማመዱ የሚያስችሉ የሥነ-ልቦናና ማህበራዊ መነቃቃት በትምህርት ቤቶችና በወላጅ ዘንድ መዘንጋቱን ነው። ይህን ክፍተት ለመሙላት መልካም የሆነ የሕፃናትና የአዋቂዎች መስተጋብር በቅድመ መደበኛ ትምህርት ማዕከላትና በቤት ደረጃ መጐልበት አለበት።

ባለፉት ሦስት አሥርት ዓመታት ውስጥ ቀዳማይ ልጅነትን በተመለከተ ከቄስ ትምህርት ቤትና ቁራን ትምህርት ቤት በተጨማሪ ሌሎች ዘመናዊ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ማዕከላት ብቅ ብቅ ማለት ጀምረዋል። እነዚህ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ማዕከላት በመንግሥትና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች፣ በማህበረሰቡ፣ በእምነት ተኮርና በግል ተቋሞች በመታገዝ ላይ ይገኛሉ። ከ80ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ በማህበረሰቡ የሚታገዙ የቀዳማይ ልጅነት ዘመን ማዕከላት እየተቋቋሙና ቁጥራቸውም እየጨመረ መጥቷል። ባለፉት ጥቂት ዓመታት የግል ዘርፉ በቅድመ መደበኛ ትምህርት ላይ መዋዕለ ንዋይ የማፍሰስ ፍላጐቱ እየጨመረ መጥቷል። ይህም በከተሞች በተለይም በአዲስ አበባ በስፋት ይታያል።

የቀዳማይ ልጅነት ዘመን ትምህርት ተሳትፎ በ2001 ዓ.ም 4.2% ብቻ የነበረ ሲሆን ይህም በከተሞች አካባቢ ተወስኖ የሚገኝ ነው።[8]

በሀገር አቀፍ ደረጃ በ2001 ዓ.ም 22.9% የሚሆኑ ተማሪዎች አንደኛ ክፍል ተመዝግበው ወደ ሁለተኛ ክፍል ሳይቀጥሉ ትምህርታቸውን አቋርጠዋል።[9] በዚህ ዓመት እስከ ስምንተኛ ክፍል ትምህርታቸውን ሳያቋርጡ የቀጠሉ ተማሪዎች 43.6% ብቻ ናቸው።

## 2.4 ለቀልዘአት እየተሰጡ ያሉ ድጋፎችና የአገልግሎት አሰጣጥ ዘዴዎች

በ1999 ዓ.ም በተካሄደ የዳሰሳ ጥናት ውጤት መሠረት በቀልዘአት ዙሪያ ካጋጠሙ ችግሮች ውስጥ ለትምህርት የሚከፈለው ገንዘብ ውድ መሆን፣ ለመምህራን ተገቢው ሥልጠና አለመሰጠት፣ ወጥ የሆነና ደረጃውን የጠበቀ ሥርዓተ ትምህርትና መመሪያ አለመኖር፣ ባህልን ያገናዘቡ የተረት-ነክ መጻሕፍት አለመገኘት፣ ለአብዛኛዎቹ ሕፃናት በተለይም ገቢያቸው አነስተኛ ከሆነ ቤተሰብ ለሚመጡ ሕፃናት የቀዳማይ ልጅነት ትምህርት የሚያገኙበት ሁኔታ አለመኖር፣ ለሕፃናት የሚሰጠው የእንክብካቤ ዓይነትና የትምህርት ጠቀሜታ በማህበረሰቡ ያለመታወቅ፣ የመምህራን የደመወዝ መጠን አነስተኛነትና ከሥራ ለመልቀቅ ምክንያት መሆን፣ የቀዳማይ ልጅነት ዘመን ትምህርት ባለሙያዎች እጥረት መኖር፣ ለሕፃናት ትምህርት የተዛባ አመለካከት መኖር እና የውጭ ቋንቋ በተለይ እንግሊዝኛን የማስተማሪያ ቋንቋ አድርጎ መጠቀም ዋናዎቹ ናቸው።

ይሁን እንጂ አሁን ባለው የቀልዘአት ትግበራ የሚገኙ ጠቃሚ ልምዶችና ዕድሎችም አሉ። ለምሳሌ እስካሁን በተገቢው መንገድ ተግባር ላይ ያልዋለ ቢሆንም ከሦስት እስከ ስድስት ዓመታት ለሚገኙ ሕፃናት ሥርዓተ ትምህርት የተቀረፀላቸው መሆኑ፣ ጥራትን የማረጋገጥና ፈቃድ የመስጠት ሥርዓት በተወሰኑ ክልሎች ሥራ ላይ መዋል፣ ምንም እንኳን ቀልዘአትን የማስተባበሩን ሚና እንደ ሁለተኛ ተግባር የመቁጠር ዝንባሌ ቢታይም በክልሎችና በከተማ አስተዳደር ቢሮዎች ውስጥ ጉዳዩን የሚመለከቱ ባለሙያዎች መኖር፣ እና ስልጠና በመውሰድ ወደ ቅድመ መደበኛ ትምህርት መምህርነት ማደግ የሚችሉ ልምድ ያላቸው መምህራን መኖር ጠቃሚ ልምዶች ናቸው። በተጨማሪም የግል ባለሀብቶች፣ የግብረ ሰናይ ድርጅቶች፣ እና የኃይማኖት ተቋማት ቀልዘአትን የማስፋፋት ፍላጐት ማሳየት መጠቀስ ያለባቸው አበረታች እንቅስቃሴዎች ናቸው። የባህላዊና ማህበራዊ ተቋማት ማለትም ዕድሮች እና ሌሎች ማህበራት ለምሳሌ የሴቶች ማህበር፣ የገበሬዎች ማህበር መኖር ወደፊት ለቀልዘአት መስፋፋት ከፍተኛ ሚና ይኖራቸዋል። በመንደር ደረጃ መሠረታዊ የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ከፍተኛ መሻሻል አሳይቷል። ነገር ግን የአፈፃፀም ችግርና የገንዘብ እጥረት መስተዋሉ አልቀረም።

8 ምንጭ፣ የቀዳማይ ልጅነት ትምህርት ገጽታ በኢትዮጵያ 1999 ዓ.ም.

9 ምንጭ፣ የትምህርት ሚኒስቴር ዓመታዊ ስታቲስቲካል ሪፖርት 2004 ዓ.ም.

# 3. የአጠቃላይ ቀልዘኢት ፖሊሲ ማዕቀፍ አስፈላጊነት

## 3.1 የቀልዘኢት ፖሊሲ ማዕቀፍ አስፈላጊነት

**ሕፃናት ያላቸውን እምቅ ችሎታ ሙሉ በሙሉ አውጥተው መጠቀም ይችሉ ዘንድ፣ አጠቃላይ የቀዳማይ ልጅነት እንክብካቤና ትምህርት የፖሊሲ ማዕቀፍ ለኢትዮጵያ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።**

በነባር ፖሊሲዎች፣ መዋቅሮች፣ ግብአቶችና እውነታዎች ላይ የተመረኮዘ እና አነስተኛ ወጪ ላይ የተንተራሰ ስትራቴጂ የቀልዘኢትን መሠረት ለመጣል ይረዳል። ይህ ደግሞ የተለያዩ የዘርፍ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችን ቀና ትብብርና እገዛን ይፈልጋል። ይህ የፖሊሲ ማዕቀፍ በዘርፉ ለሚሳተፉ ባለድርሻ አካላት የወደፊት ዕይታን የሚጠቁም ሲሆን፣ በመካከላቸው የተጣመረና የተቀነባበረ ሥርዓት በማዳበር የአፋጣኝና የመካከለኛ ጊዜ አቅጣጫን ይጠቁማል። በተጨማሪም በፖሊሲዎችና መዋቅሮች ያሉትን ክፍተቶችና ድግግሞሾችን በማስወገድ ወጪዎችን በሚቀንስ መልኩ ተቃኝተው ቀልዘኢትን ተግበራዊ ለማድረግ መንቀሳቀስ አለባቸው።

በአሁኑ ሰዓት ጨቅላና ለጋ ሕፃናትን በተመለከተ በተናጠል የሚሰጡ ግልጋሎቶች በዘርፉ መመሪያዎችና በፖሊሲ ማዕቀፍ እየታገዙ አይደለም። በተግባር እንደሚታየው በዚህ ዕድሜ ክልል የሚሰጡ ግልጋሎቶች በቂ አለመሆን ብቻ ሳይሆን የተበታተኑና ቅንጅት የጎደላቸው ናቸው። ይህም በመሆኑ ለዚሁ ዘርፍ የተመደበውን ውስን ሀብት በሚገባ ለመጠቀም አልተቻለም። በመሆኑም አብዛኞቹን ሕፃናት ተገቢ እንክብካቤና የትምህርት ዕድል አሳጥቷቸዋል። ሕፃናት ለተለያዩ ጥቃቶችና ለአደገኛ የጤና መታወክ ተዳርገዋል። ይህ ችግር በጊዜ ካልተፈታ የሀገሪቱን ዕድገት በሚወስነው የሰው ሀብት ልማት ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል። የእነዚህ ችግሮች መኖር የቀልዘኢት ፖሊሲ ማዕቀፍ በአስቸኳይ እንዲዘጋጅ አድርጎታል። በመሆኑም በዚህ የፖሊሲ ማዕቀፍ ውስጥ የኢትዮጵያ መንግሥት ለሁሉም የሀገሪቷ ሕፃናት መልካም የሕይወት ጅማሮና ቀዳሚ መነቃቃት መኖር እንዳለበት አስምሮበታል። የፖሊሲ ማዕቀፉ የተሻለ ጥራት ያለው፣ በተቀነባበረ የልማት አጋሮች ትብብርና በአቅም ግንባታ ኘሮግራሞች የታገዘ ተደራሽና ፍትሃዊ የሆነ አገልግሎት ለለጋ ሕፃናት እንዲኖር ያደርጋል።

## 3.2 የፖሊሲ አግባብ

1. በተባበሩት መንግሥታት የተደነገገውና በኢትዮጵያ የሽግግር መንግስት በ1984 ዓ.ም የፀደቀው የሕፃናት መብት ድንጋጌ እንደሚያመለክተው የሕፃናት የመማር መብት “የሕፃናትን ስብዕና፣ ተሰጥዖና እና አካላዊ ችሎታን ሙሉ በሙሉ ማበልፀግ” ላይ ማተኮር እንዳለበት ያስገነዝባል። መጋቢት 1983 ዓ.ም በጆምቴን፣ ታይላንድ የተካሄደው ዓለም አቀፍ “ትምህርት ለሁሉም” ጉባኤ ላይ “ቀዳማይ የልጅነት ዘመንን የሰው ልጅ የሕይወት መሠረት የሚጣልባቸው ዓመታት” በማለት ጠቀሜታቸውን አጉልቶ አስምሮበታል። በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ፣ የዓለም አቀፍ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ መብቶች፣ እና የሕፃናት መብቶች ስምምነት ላይ እንደተጠቀሰው የአባል ሀገራት ግዴታዎች ለሕፃናት ትምህርት ማቅረብ ላይ ብቻ የተገደበ ሳይሆን የትምህርቱን ይዘትና ጥራት ማረጋገጥንም ያካትታል።

2. የኢትዮጵያ የጤና፣ የቤተሰብ፣ የትምህርትና የማህበራዊ ዋስትና የፖሊሲ ሰነዶች በየፊናቸው የሕፃናትን ጥበቃ፣ እንክብካቤ፣ ጤናና ትክክለኛ ዕድገትን ያካተቱ ድንጋጌዎች አሏቸው። እነዚህ ፖሊሲዎች በሚከተሉት ሦስት ነጥቦች ላይ የጋራ የሆነ ዕይታ ያንፀባርቃሉ። እነዚህም፣ ሀ) ሁሉም ሕፃናት ጥሩ ዕድገት እንዲኖራቸው ከማንኛውም በሽታ፣ ከአካላዊ ወይም ሥነ-ልቦናዊ ጥቃት በመከላከልና ለሕፃናት ተስማሚ አካባቢ በመፍጠር ሁሉን አቀፍ ዕድገትን በማፋጠን ያምናሉ። ለ) የቤተሰብ አቅምን ማሳደግ ለሕፃናት የተመቻቸ ዕድገት አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ይረዳሉ። ሐ) ልዩ ጥበቃ የሚሹ ሕፃናት (የአካል ጉዳተኞች፣ በደማቸው ውስጥ የኤች. አይ. ቪ. ቫይረስ የሚገኝ፣ ወላጆቻቸውን ያጡ፣ መጠለያ የሌላቸው እና በሥራ ላይ የሚገኙ ሕፃናት) ፍላጐት በማሳካት ላይ ቁርጠኝነት አላቸው። በ1986 ዓ.ም የተቀረፀው የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ከቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋማት እስከ ከፍተኛ ትምህርት ድረስ አጠቃላይና ዝርዝር ዓላማዎችን፣ የትግበራ ስትራቴጂዎችን አካትቶ ይዟል። ቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋማት በሕፃናት ሁለንተናዊ ዕድገት ላይ በማተኮር ሕፃናቱን ለመደበኛ ትምህርት ማዘጋጀት እንዳለባቸው ይጠቁማል። እነዚህ ፖሊሲዎች በአጠቃላይ የመጀመሪያ ዓመታትን ልምዶች ጠቀሜታ ይገነዘባሉ። እነዚህ ግንዛቤዎች ጠንካራ ሕጋዊ ከለላዎች ለቀልዘኡት ከመስጠታቸው በተጨማሪ ለአጠቃላይ ቀልዘኡት ፖሊሲ ማዕቀፍ መኖር መንገድ ጠርገዋል። ይህ ደግሞ የፖሊሲ ማዕቀፉ አፈፃፀም ምን ላይ ማተኮር እንዳለበት ያስገነዝባል።

## 3.3 የቀዳማይ ልጅነት ዓመታት ዕድገት ጠቀሜታ

በቅርቡ በአዕምሮ ዕድገት ላይ የተሠሩ ጥናትና ምርምሮች የመጀመሪያዎቹ ስድስት ዓመታት ፈጣን ለሆነ የአዕምሮ ዕድገት ጠቃሚ መሆናቸውን ያመለክታሉ። በ6ኛ ዓመት መጨረሻ ላይ የአንድ ሕፃን አዕምሮ ከፍተኛ የሆነ የነርቭ ትስስር ይኖረዋል። ስለዚህ የሚጠበቀው ተግባር ይህንን የአዕምሮ ትስስር በቀዳሚ የማነቃቃት ስልትና ጥራት ባለው እንክብካቤ በመታገዝ ዘላቂነት እንዲኖረው ማድረግ ነው። በቀዳማይ ዓመታት ሕፃናት በትንሽ ጥረት በቀላሉ ዕውቀትና ክህሎትን በፍጥነት ይቀስማሉ። በዚህ ወቅት አዕምሮ ከአካባቢ በሚደረግለት እንክብካቤና ማነቃቃት ከፍተኛ ለውጥ ያሳያል። ይህ ዘመን የተስተካከለ የጤናና የአመጋገብ ድጋፍ ለመስጠት ወሳኝ ወቅት ነው።

## 3.4 በቀዳማይ ልጅነት ዓመታት ላይ የሚደረግ የመዋዕለ ንዋይ ፍሰት ጠቀሜታ

በኢትዮጵያ በጨቅላና በለጋ ሕፃናት ላይ በሚያተኩሩ ኘሮግራሞች ላይ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ ከሚያስገኘው በርካታ ጥቅሞች ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

- ለአደጋ ተጋላጭ ሕፃናት፣ ከኤች አይ ቪ ጋር የሚኖሩ ሕፃናትንና፣ ልዩ ፍላጐት ያላቸው ሕፃናትን በመለየትና ፈጥኖ የድጋፍ እርምጃ በመውሰድ የተሻሉ ዕድሎችንና ሁኔታዎችን መፍጠር ያስችላል።
- የመጀመሪያ ደረጃ የትምህርት ተሳትፎን በፍትሐዊነት ለማሳደግ ይረዳል። ምክንያቱም የቀልዘኢት ተሳትፎ ሁሉንም ሕፃናት በእኩል ለመማር የተዘጋጁ እንዲሆኑ ያደርጋል።
- ምርታማነትን ይጨምራል፤ ምክንያቱም ለወላጆች የሚደረገው ድጋፍ ጤናማና ተመጣጣኝ ምግብ ያገኙ ሕፃናትን እንዲያሳድጉ ስለሚረዳቸው ነው።
- ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ይኖረዋል፣ ምክንያቱም ከጅምሩ በሚገባ የተዘጋጁ ሕፃናት በትምህርታቸው ውጤታማ ስለሚሆኑ፣ በተለይ ገቢያቸው አነስተኛ ከሆነ ቤተሰብና ከታዳጊ ክልሎች ለሚመጡ ሕፃናት የኘሮግራሙ ተደራሽነት ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል።
- በሀገርና በቤተሰብ ደረጃ ወጪን ይቀንሳል፤ በጥራት የተንከባከቧቸው ሕፃናት ጤናማና በትምህርታቸው ውጤታማ ይሆናሉ፤ ይህም ትምህርት የሚያቋርጡትንና ክፍል ደጋሚ ተማሪዎችን ቁጥር ለመቀነስ ያስችላል።
- ድህነትን ይቀንሳል፣ ጥራት ባለው ቀዳማይ የልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት ውስጥ ያለፉ ሕፃናት በትምህርታቸው የተሻለ ውጤት ስለሚኖራቸው ወደፊት የተሻለ የሥራ ዕድል ስለሚፈጠርላቸው የተሻለ የኑሮ ደረጃ ይኖራቸዋል።
- ለሴት ሕፃናት የተሻለ ዕድል መፍጠር መቻል፤ በቀዳማይ ልጅነት ዘመን በሚገባ ለትምህርት የተዘጋጁ ሕፃናት ወደ መጀመሪያና ከፍተኛ መደበኛ ትምህርት የመቀጠል ዕድላቸው የሰፋ ይሆናል።
- የቤተሰብ ደህንነትን ያሻሽላል፣ ወላጆችና ማህበረሰቡ የተሻለ ዕውቀትና ክህሎት ሲያገኙ መልካም ዝንባሌ ስለሚኖራቸው የቤተሰብ ደህንነት አብሮ ይሻሻላል።
- የወላጅና የህብረተሰብ አቅምን የማጎልበት ዕድል ይሰጣል።

# 4. የቀልዘእት ፖሊሲ ማዕቀፍ

## 4.1 ራዕይ

ሁሉም ሕፃናት ጤናማ የሕይወት ጅማሬ የማግኘት፣ ደህንነታቸው በተጠበቀ ሁኔታ የማደግ፣ ተንከባካቢና አነቃቂ አካባቢ የማግኘትና እምቅ ችሎታቸውን በተሟላ ሁኔታ የመዳበር መብታቸው ተረጋግጦ ማየት ነው።

## 4.2 ተልዕኮ

1. ሁሉን አቀፍ፣ የተቀናጀ፣ ጥራት ያለው፣ ከዕድገትና ከአካባቢው ጋር የተጣጣመ አገልግሎት በመስጠት የሕፃናቱን ሁለንተናዊ ዕድገት ማበልፀግ፤
2. የእያንዳንዱን ሕፃን ባህልና ቋንቋ ባከበረና ባረጋገጠ መልኩ ሕፃናት እምቅ ችሎታቸውን በሙሉ አቅም የሚያሳድጉበት መሠረት መጣል፤
3. ልዩ ፍላጐት ያላቸውንም ጨምሮ የሁሉንም ሕፃናት መብቶችና ደህንነት ማረጋገጥና መጠበቅ።

## 4.3 የቀልዘእት ፖሊሲ ማዕቀፍ መሪ መርሆዎች

የቀልዘእት ፖሊሲ በሚከተሉት መርሆዎች ይመራል።

1. የሀገራችንን ባህላዊ ዕሴቶች፣ የወላጅና የህብረተሰቡን ተሳትፎ መጠበቅና ማሳደግ፣
2. የለጋ ሕፃናት ሁለንተናዊ ፍላጐቶች መሟላታቸውን ማረጋገጥ፣
3. ፍትሀዊ፣ ተደራሽነትና ጥራት ያለው ቀልዘእት ለሁሉም ሕፃናት ማዳረስ፣
4. የአካትቶ ዘዴን በመጠቀም ለችግር ተጋላጭና የተገለሉ ሕፃናትን በተለይ ልዩ ፍላጐት ያላቸውን መድረስ መቻል፣
5. በሕፃናት እንክብካቤ፣ መብቶች፣ ጤና፣ ትምህርትና ዕድገት ላይ በሚሠሩ ተዛማጅ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች መካከል የተቀናጀ ትብብር መፍጠር፣
6. ማህበረሰብን መሠረት ባደረገ አቀራረብ ወጪ ቆጣቢና ተፈፃሚነት ያለው ዕቅድ ከግልፅ የድርጊት መርሀ-ግብር ጋር በማዘጋጀት ሁሉም ሕፃናት መደበኛ ት/ቤት ከመግባታቸው በፊት የቀልዘእት አገልግሎት ማግኘት የሚችሉበትን መንገድ ማመቻቸት፣
7. ቀልዘእት ከቅድመ ወሊድ እስከ ሰባት ዓመት ያሉትን የሕፃናት ፍላጐት ለማሟላት ይሠራል፣
8. ቤተሰብ ለልጅ ሁለንተናዊ ዕድገት የመጀመሪያ ኃላፊነት የተጣለበት ማህበራዊ ተቋም ነው፤ በመሆኑም ወላጆች ሚናቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ሙያዊ እገዛ ይደረግላቸዋል።

## 4.4 ግቦችና ስትራቴጂያዊ ዓላማዎች

የፖሊሲ ማዕቀፉ አጠቃላይ ግብ በውጤታማ አጋርነትና በአቅም ግንባታ ኘሮግራሞች ላይ በመመሥረት ከቅድመ ውልደት እስከ ሰባት ዓመት ያሉ ሕፃናት ጥሩ የሕይወት ጅማሬ እንዲኖራቸው ማድረግ፣ የቀልዘኢትን ጥራት ማሻሻልና ማሳደግ፣ ፍትሐዊ አገልግሎትን፣ ተደራሽነትንና ስርጭትን ማረጋገጥ ነው።

የፖሊሲ ማዕቀፉ ስትራቴጂያዊ ዓላማዎች ትኩረት፤

ሀ. ለቀልዘኢት ተያያዥ የአስተዳደር መዋቅር መዘርጋትና ቀልዘኢት በሁሉም ተዛማጅ ብሔራዊ ፖሊሲዎችና ኘሮግራሞች መካተቱን ማረጋገጥ፤

ለ. ተደራሽ፣ ፍትሐዊና ጥራት ያለው የቀልዘኢት አገልግሎትን ለሁሉም ሕፃናት በተለይ ለችግር ተጋላጭ ለሆኑ፣ ልዩ ፍላጐት ላላቸውና ለተገለሉ ሕፃናት ልዩ ትኩረት በማድረግ ለመስጠት ተገቢውን ዕገዛ ማድረግ።

ሐ. ለጋ ሕፃናትን ከማንኛውም ዓይነት ጥቃትና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች መጠበቅ፣

መ. ለሕፃናት የሚሰጡ አገልግሎቶችና ኘሮግራሞች ውጤታማ እንዲሆኑ ለማድረግ የሁሉም ባለድርሻ አካላት አጋርነትና ትብብርን ማሳደግና ማጠናከር፣

ሠ. ከቅድመ ወሊድ እስከ ሰባት ዓመት ላሉ ሕፃናት ጥራት ያለው አገልግሎት መሰጠቱን ለማረጋገጥ ማቀድ፤ አስፈላጊውን ሃብት መመደብ እንዲሁም ማንቀሳቀስ ላይ ነው።

## 4.5 መዋቅራዊ አደረጃጀትና የተግባራት ትኩረት

በኢትዮጵያ ቀልዘኢት የሚሸፍነው ከቅድመ ወሊድ እስከ 7 ዓመት የዕድሜ ክልል ያሉትን ሕፃናት ነው። የዕድገት ደረጃ ፍላጐቶችን ለመግለፅ ሁለት የዕድሜ ደረጃዎች ጥቅም ላይ ውለዋል። እነዚህም ከቅድመ ወሊድ እስከ 3+ዓመትና ከ4-7 ዓመት ያሉት የዕድገት ደረጃዎች ናቸው። በነዚህ ደረጃዎች የሕፃናቱን ሁለንተናዊ ዕድገት የሚያፋጥን ኘሮግራም ማለትም፣ ሕፃናቱ አካባቢያቸውን በመዳሰስ ባህሪያቸውን የሚገልጹበት፣ የእንቅስቃሴ ዕድገታቸውን የሚፈትሹበት፣ ሥነ-ልቦናቸውንና ስሜታቸውን የሚገልጹበት፣ ማህበራዊና የመግባባት ክህሎታቸውን የሚያዳብሩበት ኘሮግራም መቅረፅ ቀላል አይደለም። የመነሻ ጥናቱ እንደሚያሳየው በኢትዮጵያ ቀልዘኢት ገና በማደግ ላይ የሚገኝ ኘሮግራም ነው። ብዙ ወላጆች በልጆቻቸው ዕድገት ላይ ያላቸውን ወሳኝ ሚና አልተገነዘቡም ወይም ልጅ የማሳደግ ብቃት ያንሳቸዋል። በዚህ ወቅት አጠቃላይ የሆነ የቀልዘኢት አገልግሎት ተደራሽነትም እጅግ በጣም ውስን ነው። ሁሉን አቀፍ ሥርዓት በሀገሪቱ ገና አልተዘረጋም። ያሉት አገልግሎቶች ለምሳሌ እንደ ጤናና ትምህርት የመሳሰሉት ተጠቃሚነትም ውስን ነው። በመሆኑም የፖሊሲው ግቦች ሙሉ በሙሉ ከመረጋገጣቸው በፊት የተወሰኑ ዓመታት ሊያስፈልጉ ይችላሉ።

ከፅንስ እስከ 7 ዓመት የሚሸፍን የቀልዘእት አገልግሎት በአጠቃላይ ለመተግበር የተሻለና ወጪ ቆጣቢ መንገድ ማዘጋጀት ያስፈልጋል። ለዚህም በጥናትና በውይይት የተደገፈ የመነሻ ሰነድ ተዘጋጅቷል። በዚህም መሠረት የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከቅድመ ወሊድ እስከ 3+ዓመት በኃላፊነት ይመራል። በዚህ ወቅት የጤና፣ የሥነ-ምግብና የቀዳሚ ማነቃቃት ትምህርት ለወላጆች ይሰጣል። ይህ ለሕፃናቱ ሁለንተናዊ ዕድገት በጣም አስፈላጊ ነው። ከ4-7 ዓመት ላለው ወቅት የትምህርት ሚኒስቴር ኃላፊነቱን ይወስዳል። በዚህ ጊዜ ሕፃናት የቅድመ መደበኛ ትምህርት የሚጀምሩበት ወቅት ነው። የሕፃናትን ሁለንተናዊ ዕድገቶች ማለትም የአካል፣ የአእምሮ፣ የሥነ-ልቦና፣ የማህበራዊና የቋንቋ ክህሎትን የሚዳብሩበት ወቅት ነው።

### 4.5.1. የቀልዘእት አገልግሎት መሠረታዊ ምሰሶዎች

ቀልዘእት በኢትዮጵያ አራት መሠረታዊ ምሰሶዎች ይኖሩታል። እነዚህም፡-

ሀ. የወላጅ/አሳዳጊ ትምህርት፣

ለ. የጤናና ቀዳሚ ማነቃቂያ ኘሮግራም (ከቅድመ ወሊድ እስከ 3+ ዓመት)፣

ሐ. ቅድመ መደበኛ ትምህርት (4-7 ዓመት)፣

መ. መደበኛ ባልሆነ መንገድ ለትምህርት ቤት ዝግጁነት ኘሮግራም ናቸው።

የሕፃናትን የመማር ልምድ ከፍ ለማድረግ ጨዋታ እንደ ዋና ማስተማሪያ ዘዴ ጥቅም ላይ ሊውል ይገባል። የሕፃናትን ችሎታ ለማበልፀግ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ዓይነተኛ መሣሪያ እንደሆነ ይታመናል። በመሆኑም የአፍ መፍቻ ቋንቋ ወይም በአካባቢው የሚነገር ቋንቋ ለመምህራን፣ ለአሳዳጊዎችና ሕፃናት መግባቢያነት ይውላል።

#### 4.5.1.1 የወላጅ ትምህርት

የወላጅ ትምህርት ተከታታይ፣ ቀጣይና የረጅም ጊዜ ተግባር ሆኖ የሚያተኩረውም የወላጆችን ግንዛቤ በማሳደግና በማጎልበት ላይ ነው። ሁሉም ወላጆች ልጆቻቸውን ለማሳደግ ያለባቸውን ኃላፊነት ተወጥተው ውጤታማ እንዲሆኑ አቅማቸውን ማጎልበት ያስፈልጋል። የወላጆች ትምህርት የሚያተኩረው የወላጆችንና አሳዳጊዎችን ተግባራዊ የልጅ አስተዳደግ ክህሎትን ማሻሻል ላይ ነው። ትምህርቱ የሚያጠቃልለውም የቅድመ ወሊድ፣የወሊድና የድህረ ወሊድ እንክብካቤን ነው። ወላጆች የሕፃናት ዕድገት ሂደትን፣ የጥሩ ጤና እንክብካቤና አያያዝን፣ አመጋገብን፣ ንጽህና አጠባበቅና የቀዳሚ ማነቃቃት ዘይቤን በሚገባ እንዲገነዘቡ በማድረግ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ሁኔታዎች ይመቻቻሉ። የወላጅ ትምህርት ብቻውን የቆመ የእገዛ ሥርዓት አይደለም። ይልቁን በሦስቱም ዋና ዋና ምሶሶዎች ውስጥ መካተት ያለበት ጠቃሚ ተግባር ነው። የወላጆች ትምህርት የጤና ኤክስቴንሽን ኘሮግራም አካል ነው። ትምህርቱም በጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ተቆጣጣሪነት በማህበረሰብ አቀፍ ጤና መልዕክተኞችና በሞዴል ቤተሰቦች ሊተገበር ይችላል። በተጨማሪም የወላጅ ትምህርት ከጐልማሶች ትምህርት ኘሮግራም ጋርም ሊቀናጅ ይችላል።

የወላጅ ትምህርትና የማሳያ ፕሮግራም፣ በቤትና በማዕከል ሊተገበር ይችላል። በቤት ውስጥ የሚተገበረው በእያንዳንዱ ቤተሰብ መኖሪያ ቤት ውስጥ ሊከናወን ይችላል። ማዕከልን/ጣቢያን መሠረት ያደረገው በማንኛውም የህብረተሰብ አገልግሎት መስጫ ሕንፃ ማለትም የጤና ኬላ፣ ት/ቤት፣ ቤ/ክርስቲያን/መስጊድ፣ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ጣቢያ ወዘተ ላይ ሊከናወን ይችላል። መገናኛ ብዙኃንም በተቻለ መጠን ድርሻቸውን የሚወጡበት መንገድ ይፈለጋል።

በመንደር ደረጃ ለወላጆች ትምህርቱን የመስጠት ኃላፊነቱ የሚወድቀው በቀበሌ ጤናና ትምህርት ቦርድ ላይ ነው። በብሔራዊና ክልላዊ ደረጃ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የሥልጠና መመሪያ፣ የትምህርት መርጃና የአሠልጣኞች ሥልጠናን የማዘጋጀት ኃላፊነት አለባቸው።

### 4.5.1.2 ጤናና የቀዳሚ ማነቃቂያ ፕሮግራም (ቅድመ ወሊድ-3+ ዓመት)

አሁን ያለው የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ለሁሉም ከቅድመ ወሊድ እስከ 3+ዓመት ላሉ ሕፃናትና ለወላጆቻቸው የተቀናጀ አገልግሎት ይሰጣል። የዕድገት ዘርፎች የማነቃቃት ተግባራትም አብረው ይከተታሉ። ይህ አገልግሎት የቤተሰብ ጤና ማዕቀፍ ክፍል ሆኖ በጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችና በማህበረሰብ አቀፍ ጤና መልዕክተኞች በቤት ወይም በማዕከል ሊሰጥ ይችላል። በቅርብ ያለው የጤና ጣቢያ ለጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ቴክኒካዊ ድጋፍ የመስጠት ኃላፊነት አለበት። በጣቢያ/ማዕከል የሚሠራው ክፍል በተቻለ መጠን ጤና ኬላዎችን መጠቀም አለበት። ጤና ኬላ በሌለባቸው አካባቢዎች ያሉትን የህብረተሰብ ማዕከላት፣ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች፣ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች ወዘተ. መጠቀም ይኖርባቸዋል። ወላጆቻቸው ከሕፃናት አስተዳደግና እንክብካቤ ጋር የተያያዘ ትምህርት ሲማሩና በገለፃ ፕሮግራም ሲካፈሉ ሕፃናት ከሌሎች እኩዮቻቸው ጋር የሚጫወቱባቸው ቦታዎች ሊመቻቹ ይገባል።

በነዚህ ፕሮግራሞች ተጠቃልለው የሚሰጡት የዕድገትና የጤና ክትትል፣ የዕድገት ፍላጐት ማሟላት፣ የጤና አጠባበቅ እንክብካቤ፣ ሙሉ ክትባት፣ የምግብ እገዛ፣ ቀዳሚ ማነቃቃት፣ የወላጆች ትምህርትና ገለጻ ናቸው። እነዚህ ተግባራት ከቀዳሚ ማነቃቃት በስተቀር በቤተሰብ ጤና ማዕቀፍ ተካተዋል። የቀዳሚ ማነቃቂያ ተግባራት ሰነድ ተቀርፆ በቤተሰብ ጤና ማዕቀፍ ውስጥ መካተት አለበት። የማህበረሰብ የጤና ቀናት ይዘጋጃሉ። በእነዚህም ቀናት የምግብ እጥረት ያለባቸውን ሕፃናት የመለየትና የጥቃቅን ንጥረ ምግቦች (micro nutrients) ዕደላ ይከናወናል። ከቅድመ ወሊድ - 3+ ዓመት ያለው ዘመን ለሕፃናት አዕምሮ ዕድገት ወሳኝ በመሆኑ ለጋ ሕፃናት ላልተመጣጠነ ምግብ ወይም የምግብ እጥረት ተጋልጠው በሕይወታቸው ዘላቂ ጉዳት ከመድረሱ በፊት መከላከል አስፈላጊ ነው። ፕሮግራሙ ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው በጐልማሶች እንክብካቤና በጎልማሳና ሕፃን መስተጋብር ጥራትና በቀዳሚ ማነቃቃት ላይ በቤተሰብና በህብረተሰብ ደረጃ ትኩረት ሰጥቶ ይሰራል።

የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ከማህበረሰብ አቀፍ ጤና መልዕክተኞች ጋር በመሆን በጤና ኬላና በሌሎች የህብረተሰብ ጣቢያዎች በቤትና በማህበረሰብ ደረጃ ለሚሠሩት ተግባራት ኃላፊነት አለባቸው። የወረዳ ጤና ጽ/ቤቶች ለጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ድጋፋዊ ክትትል ያደርጋሉ። እንዲሁም የጤና ኬላውን አጠቃላይ አስተዳደር ይከታተላሉ። ማህበረሰቡ ከጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምና ከጤና ኬላዎችና ከቀበሌ የጤና ኮሚቴ ጋር ኃላፊነት ይጋራል።

### 4.5.1.3 ቅድመ መደበኛ ትምህርት (4-7 ዓመት)

የቅድመ መደበኛ ትምህርት ማዕከላት ኘሮግራም የሚያተኩረው ሕፃናት መሠረታዊ ክህሎቶችን (ቅድመ ንባብ፣ ጽሕፈት፣ ቆጠራና ሒሳብ) እንዲያዳብሩና ለመደበኛ ት/ቤት ዝግጁ እንዲሆኑ በማድረግ ላይ ነው። የማህበራዊና ስሜታዊ ብቃት፣ ራስን የመቆጣጠር፣ ውስጣዊ የመማር ፍላጐት መቀስቀስና ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መተባበርን የመሳሰሉትን ክህሎት ሕፃናት በቀዳማይ የልጅነት ትምህርት ማዕከላት የሚያገኟቸው ሌሎች ጥቅሞች ናቸው። ከዚህም ሌላ ቅድመ መደበኛ ትምህርት ማዕከላት ሕፃናት እንደ እጅ መታጠብና መልካም የአመጋገብ ልምድ ያሉ መሠረታዊ የሕይወት ክህሎትን የሚማሩበት ቦታ ነው። ከፊታችን ነገሮች አንዱ ከላይ የተዘረዘሩትን የዕድገት ዘርፎችና የክህሎት ብቃቶች በኩል ሊያዳብር የሚችል ሥርዓተ-ትምህርት መቅረፅና መተግበር ነው። ይሁን እንጂ ኘሮግራሙ ሕፃን ተኮርና የሕፃናትን ሁለንተናዊ ዕድገት የሚያበለፅግ መሆን አለበት። ይህን ለማሳካት የትምህርት ኘሮግራሙ የባህል አግባብነት ያለው፡ ለዕድገት ተገቢና ከክፍል ውስጥና ከክፍል ውጭ አስፈላጊ ቁሳቁሶችንና ተግባራትን ያካተተ ይሆናል። ኘሮግራሙ ሲቀረፅ ጨዋታን መሠረት ያደረገ አቀራረብ መከተል ይኖርበታል።

የማህበረሰብ አቀፍ ቅድመ መደበኛ ትምህርት ማዕከል ከፍተኛ ጥራት ያለው የወላጅ/ሞግዚት ሕፃን መስተጋብርን ለማሳደግ ይሠራል። ወላጆች የጨዋታን ጠቀሜታ አውቀው ጥቅም ላይ ሲያውሉት ልጆቻቸው በትክክለኛው ዕድሜ ወደ ት/ቤት ለመሄድ ዝግጁ ሆነው ያገኟቸዋል።

የቅድመ መደበኛ ትምህርት ማዕከል ለሕፃናቱ ምቹና የማያሰጋ አካባቢ መሆን አለበት። የመምህራንና ወላጆች/ሞግዚቶች የጋራ ተሳትፎና ውይይት ለሕፃናቱ ዕድገት ሂደትና በቤተሰብ ውስጥ ለሚያስፈልጋቸው እገዛና ክትትል እጅግ ጠቃሚ ናቸው።

የቅድመ መደበኛ ትምህርት ማዕከላት መምህራን ለቀዳማይ ልጅነት ትምህርት ኘሮግራም ኃላፊነቱን ቢወስዱም፣የጤና ሠራተኞች የሕፃናትን፣የወላጆችንና የመምህራንን የጤና ግንዛቤ በማሳደግ በኩል ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ። የሙሉ ክትባት ኘሮግራሞች፣የዕድገት ክትትል፣የበሽታ መከላከልና የጤና ክብካቤ በቀዳማይ የልጅነት ትምህርት ኘሮግራሞች ውስጥ ይካተታሉ።

ቅድመ መደበኛ ትምህርት ማዕከላት በሌለባቸው አካባቢዎች የሚገኙ ተስማሚ ሕንፃዎች፣ የማህበረሰብ ጣቢያዎች፣ ቤተክርስቲያኖች፣ መስጊዶች፣ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ማዕከላትና የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ግቢዎች ወዘተ. ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ። በአንዳንድ ሁኔታዎች የመደበኛ ት/ቤት መማሪያ ክፍሎችን ጥቅም ላይ ማዋል ይቻላል። ህብረተሰቡ በራሱ ተነሳሽነት መደበኛ ያልሆነ ቅድመ መደበኛ ትምህርት ማዕል ከአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ጣቢያ ጋር ወይም ከማንኛውም የማህበረሰብ ጣቢያ ወይም መጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ጋር አያይዞ ሊያቋቁም ይችላል። የቀልዘእት ፖሊሲ ማዕቀፍ እነዚህንና የመሳሰሉ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉትን መሠረተ ልማቶች በተቻለ መጠን መጠቀምን ያበረታታል፣ ይደግፋል።

ትምህርት ሚኒስቴር የቅድመ መደበኛ ትምህርት ማዕከላት ሥርዓተ ትምህርት የመቅረፅ፣ ለመምህራን የቅድመ መደበኛ ትምህርት ስልጠናን የመስጠት፣ የመጫወቻና ማስተማሪያ ቁሳቁሶችን የማዘጋጀት እንዲሁም ቁጥጥርንና ጥራትን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት።

የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤቶችም ለትምህርት ቤቶቹ/ማዕከላቱ የትምህርት መሣሪያዎችን የማቅረብ ኃላፊነት አለባቸው። ጤናን ለተመለከቱ ጉዳዮች የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በየደረጃው ያሉ መዋቅሮች ኃላፊነት ነው። የሴቶች ማህበር አባላት የሴቶችንና ሕፃናትን የነቃ ተሳትፎ ለማዳበር ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ። ስለዚህ የሴቶች ማህበራት የቀልዘእት አገልግሎቶችን ለማስፋፋት የሚያስችል አቅም እንዲያዳብሩ መርዳት ወሳኝ ነው።

### 4.5.1.4 መደበኛ ባልሆነ መንገድ ለትምህርት ቤት ዝግጁነት ኘሮግራም

የተነደፈው መዋቅር ሥራ ላይ እስኪውል ድረስ ሌላ መደበኛ ያልሆነ እንደ ልጅ-ለ-ልጅ የመሰለ ዘዴን በጥቅም ላይ ማዋል ይቻላል። የልጅ-ለ-ልጅ ዋናው ዓላማ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ተማሪ ልጆች (ወጣት አመቻቾች) ታናናሽ ወንድሞቻቸውን፣ እህቶቻቸውንና የጎረቤት ሕፃናትን በጨዋታ መልክ ለመደበኛ ትምህርት ቤት እንዲዘጋጁ ማድረግ ነው። ይህን የሚሠሩት በራሳቸው ቤት ወይም ከተሳታፊ ልጆች መካከል በአንዱ ቤት ውስጥ እና በአካባቢው ጥላስር ሊሆን ይችላል። ተግባራቱ በተቻለ መጠን የአካባቢውን ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያስገቡ የሕፃናቱን የዕለት ተዕለት ሕይወት ያገናዘቡ መሆን አለባቸው።


ወጣት አመቻቾች በመምህራኖቻቸው የሰለጠኑና ድጋፍ የሚደረግላቸው የ5ኛና 6ኛ ክፍል ተማሪዎች ቢሆኑ ይመረጣል። መምህራን አመቻቾችን ከማሰልጠን ባሻገር ኘሮግራሙን በማስተባበርና በመከታተል ረገድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ። የቀን ተቀን ተግባሩን መምራት በቅርብ የሚገኘው የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ር/መምህርና የወላጅ መምህር ህብረት ኃላፊነት ነው። ወላጆችም በበኩላቸው ምልከታና ክትትል ያደርጋሉ። የልጅ-ለ-ልጅ እንቅስቃሴ ዋና ዓላማ ለጋ ሕፃናትን ለመደበኛ ት/ቤት ዝግጁ ማድረግ ነው። ሌሎች ወጪ ቆጣቢ ዘዴዎችም ወደፊት ተነድፈው ተግባራዊ ይደረጋሉ። በአጠቃላይ መደበኛ ያልሆነ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ኘሮግራም ማደራጀት የትምህርት ሚኒስቴር ኃላፊነት ነው።

## 5. ለቀልዘአት አገልግሎቶች አፈፃፀም የትብብር መዋቅር

ለቀልዘአት ወሳኝ የስኬት መሠረት የሚሆነው ሁሉንም ተሳታፊ ክፍሎች በአንድ ዓይነት የትብብር፣ የሥራ መንፈስና አስተሳሰብ መሥራትና ተከታታይ የመሻሻልና የፈጠራ ሥራን ማነቃቃት ሲቻል ነው። የበጀት እጥረት ለሚቀጥሉት ተከታታይ ዓመታት በዚህ ዘርፍ እንደ ችግር መከሰቱ የማይቀር ስለሆነ ከወዲሁ አጠቃላይ ዕቅድና በጀት መሠራት አለበት። በመሆኑም ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ውጤታማና ቀልጣፋ አስተዳደራዊ መዋቅር መዘርጋት አስፈላጊ ነው። ከዚህ በታች ይህ የፖሊሲ ማዕቀፍ የተዘጋጀበትን ሂደት የተከተለ የትብብር መዋቅር ቀርቧል። ይህን በተግባር ለመተርጐም ሁሉን አቀፍ የቀልዘአት ትግበራ ኘሮግራም መዘርጋት አስፈላጊ ነው። የስቲሪንግ ኮሚቴ ለሁሉም የቀልዘአት ተግባራት ክንውን እንደ መሪ እና ውሳኔ ሰጪ አካል ሆኖ ያገለግላል። አንድ ከፍተኛ ብቃት ያለው ባለሙያ የቀልዘአት አስተባባሪ ሆኖ ይመደባል። እርሱ/እርሷ የግብረኃይሉ ሊቀመንበርና የቀልዘአት አስተባባሪ ይሆናል/ትሆናለች። የእያንዳንዱ ተሳታፊ /ተባባሪ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤት የቀልዘአት ክፍል ይኖረዋል። የክፍሉ ተጠሪም የግብረ ሀይሉ አባል ይሆናል። ግብረኃይሉ የሚሰራው በስቲሪንግ ኮሚቴው በተሰጠው ኃላፊነት መሰረት ነው። ግብረኃይሉ ኘሮፖዛል የማዘጋጀት፣ ለስቲሪንግ ኮሚቴው የውሳኔ ሐሳብ የማቅረብ፣ የዕቅድ አፈፃፀምን የመከታተልና የመገምገም ኃላፊነት አለበት።

በክልል፣ በወረዳና በቀበሌ ደረጃ የፌደራል አደረጃጀት መዋቅሩ ወደታች በቀጣይነት ይወርዳል። ሦስቱ ተሳታፊ /ተባባሪ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች አብረው ይሠራሉ። ይሁን እንጂ አንድ ኃላፊነት የሚወስድ አካል ይኖራል። እንዲሁም እንደክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ሌሎች የሚመለከታቸውን አካላት በተጨማሪነት ማካተት ይቻላል። በማህበረሰብ ደረጃ በቀበሌ ባለው መዋቅር መሥራት ይቻላል። የቀበሌ ቀልዘአት ትግበራ ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል።

- የቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት
- የሴቶች ማህበራት
- የገበሬዎች ማህበራት
- የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች
- የወጣት ማህበራት
- የቀበሌ ትምህርትና ስልጠና ቦርድ
- የቀበሌ ጤና ኮሚቴና
- የሕፃናት መብቶች ስምምነት ኮሚቴ።




ሥዕል1፡ የቀልዘአት አገልግሎት አፈፃፀም የትብብር መዋቅርቁልፍ፡ የሴሕወጉሚ-ሴቶች ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴርክትቢ - ክልል ትምህርት ቢሮ

ይህንን ኘሮግራም በብቃት ለመምራት እንዲቻል በአዲሰ አበባ ዩኒቨርሲቲና በሌሎች የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የቀልዘአት የልኅቀት ማዕከላት ይቋቋማሉ። ይህ ማዕከል የክትትል፣ የግምገማ፣የምርምርና የፈጠራ፣ የአሠልጣኞች ሥልጠናና በቀልዘአት የከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና ኘሮግራም የማዘጋጀት ኃላፊት ይኖረዋል።

# 6. በቀልዘአት አገልግሎት አቅርቦት የአጋሮች ሚናና ኃላፊነት

የቀልዘአት አመራር፣ አገልግሎትና ኘሮግራም በተለያዩ የሚኒስቴር መስሪያቤቶች፣ ዘርፎችና ድርጅቶች በተቀናጀ መንገድ የሚመራ ይሆናል። አጋሮች ቀልዘአትን ለመተግበር ተቀራርበው በጋራ መሥራት አለባቸው። ትብብሩ በአጠቃላይ በፖሊሲ ማዕቀፉ መሠረት ቁጥጥርና ክትትል ሊደረግበት ይገባል። የዋና ዋና ባለድርሻ አካላት ተግባራትና ኃላፊነት የሚከተሉትን የሚያካትት ይሆናል።

## 6.1 ወላጆችና አሳዳጊዎች

ወላጆችና አሳዳጊዎች በሕፃናት ሕይወት ውስጥ በጣም ወሳኝ ድርሻ ያላቸው በመሆኑ በልጆቻቸው ዕድገት ላይ ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ። ሚናቸውም የሕፃናቱን ማህበራዊ ሕይወት ማሳደግ እንዲሁም ለሕፃናት መልካም ባህርይ፣ የሕይወት ክህሎትን መንፈሳዊነትን፣ ባህልንና ሥነ-ምግባርን ማስተማር እና የመሳሰሉ ናቸው። ለሕፃናት ዕድገት ምቹ የሆነ አካባቢን የመፍጠርና ቀዳሚ ማነቃቃትን የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው። በተጨማሪም የሕፃናቱ መሰረታዊ ፍላጐት መሟላቱን፤ የተመጣጠነ ምግብና የጤና እንክብካቤ ማግኘታቸውን ክትባትና የዕድገት ክትትል የተደረገላቸው መሆኑን መከታተልና ማረጋገጥ አለባቸው። የሕፃናቱ ልደት መመዝገቡን፣ የአካል ጉዳት ካለም ቀደም ብሎ መለየቱንና ድጋፍ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል። ወላጆችና አሳዳጊዎች የሕፃናትን መብቶች ማክበርና ማስከበር፣ የትምህርትና የጨዋታ ቁሳቁሶችን ማቅረብና ሕፃናቱን ከቀልዘአት አገልግሎት ጋር በጊዜው ማገናኘት አለባቸው። ወላጆችና አሳዳጊዎች የማህበረሰብ አቀፍ ጤና ኤክስቴንሽን ኘሮግራም፣ የማህበረሰብ አቀፍ ቅድመ መደበኛ ትምህርት ማዕከልና መደበኛ ያልሆነ የት/ቤት ዝግጁነት ኘሮግራም አባል ናቸው።

## 6.2 ማህበረሰብ

ማህበረሰቡ ወላጆችና አሳዳጊዎች ለልጆቻቸው ሁለንተናዊ የዕድገት ፍላጐቶች መሟላት የሚያደርጉትን ጥረት ይደግፋል። ማህበረሰቡ የቀልዝአት አገልግሎት ለሕፃናት ተደራሽ እንዲሆን፣ ከአደጋ ነፃ አካባቢ እንዲኖርና አስፈላጊ ቁሳቁሶች እንዲቀርቡ ያደርጋል። ማህበረሰቡ የሕፃናት መብቶችን ይጠብቃል፣ እንዲሁም የሕፃናትን ሁለንተናዊ ዕድገት ለማፋጠን የሚረዱ ድጋፎችን ለማግኘት ይንቀሳቀሳል። ማህበረሰቡ የተዘነጉ ሕፃናትን ፍላጐት በቀበሌው/በአካባቢው/ ያሟላል፣ ለለጋ ሕፃናት አገልግሎት ይሰጣል፤ ከሌሎች አገልግሎት ሰጪዎችም ጋር ይገናኛል፤ ይተባበራል። በተጨማሪም የለጋ ሕፃናት መብት እንዲከበር ጥብቅና ይቆማል። ለሕፃናት እንክብካቤ፣ ጤናና አመጋገብ አማራጭ አቀራረቦችን ያመቻቻል።

የማህበረሰቡ መሪዎች የማህበረሰብ አቀፍ ጤና ኤክስቴንሽን ኘሮግራም፣ የማህበረሰብ አቀፍ ቅድመ መደበኛ ትምህርት ማዕከል እንዲሁም መደበኛ ያልሆነ የትምህርት ዝግጁነት የቀበሌ ቦርድ አባላት ናቸው። ከማህበረሰብ ጋር የሚደረግ ውይይትና ምክክር ለሕፃናት እንክብካቤና ዕድገት ጠቃሚ ነው። በተለይ ከጤና ኤክስቴንሽን ኘሮግራም ጋር ተቀናጅቶ እንዲካሄድ ማድረጉ ውጤታማ እንደሚሆን ይታመንበታል።

## 6.3 የትምህርት ሚኒስቴር

ትምህርት ሚኒስቴር በቀልዘአት ላይ የፖሊሲ መመሪያዎችን ያወጣል፣ ለቀልዘአት መምህራንና አሠልጣኞች የምሥክር ወረቀት ይሰጣል፣ የመማሪያ ቁሳቁሶችን ያዘጋጃል፣ እንዲሁም ደረጃዎችንና ጥራትን ያረጋግጣል። የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ለቀዳማይ ልጅነት ዘመን ትምህርት የሥልጠና አገልግሎት ይሰጣል፣ሥርዓተ ትምህርት ያዘጋጃል፤ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ኘሮግራምና መደበኛ ያልሆነ የት/ቤት መዘጋጃ ተነሳሽነትን ይቆጣጠራል። በክልል ደረጃ ያሉ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ማዕከላትና መደበኛ ያልሆነ ት/ቤት ዝግጁነት ፕሮግራሞችን ይመዘግባል። ቀዳሚ ማነቃቃትን በተመለከተ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ጎን ለጎን የወላጆች ትምህርት መማሪያ ማስተማሪያ ያዘጋጃል። በክልል ደረጃ ልዩ ፍላጐት ያላቸውን ሕፃናት የመለየት፣ የማሰስና የማነቃቃት ሥራ የትምህርት ሚኒስቴር ኃላፊነት ነው። ትምህርት ሚኒስቴር የአቅም ግንባታና የቅስቀሳ ሥራዎችን በመሥራት ግንኙነቶችን በማመቻቸትና ትስስሮችን በማጠናከር ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። የትምህርት ሚኒስቴር የብሔራዊ የቀልዘአት ፖሊሲንና የቀልዘአት ስትራቴጂ ዝግጅትና ትግበራን ያስተባብራል። የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ለክፍል ውስጥና ውጭ ለሚያስፈልጉ የሕፃናት ማስተማሪያና መጫወቻ ቁሳቁሶች አቅርቦት መሟላት ኃላፊነት አለበት።

## 6.4 የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የጤና ባለሙያዎችን በማሠልጠን የአቅም ግንባታ ሥራዎችን መስራትና የማህበረሰብ ንቅናቄ ማካሄድ ይጠበቅበታል። በጤና ኤክስቴንሽን ኘሮግራም አማካይነት ለእናቶች፣ ለአራስ ሕፃናትና ለማህበረሰቡ ጤና አጠባበቅ ለማድረስ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ቁልፍ ሚና ይጫወታል።ለእናቶችና ለሕፃናትም ልዩ ትኩረት ይሰጣል። ከጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጆች ውስጥ የቤተሰብ ጤና ፓኬጅ አንዱ ነው። ይህም የእናቶችና ሕፃናት ጤና፣ የቤተሰብ ዕቅድ፣ ክትባት፣ ምግብና የወጣቶች ተዋልዶ ጤና ጉዳይን ያካተተ ነው። ቀዳሚ ማነቃቃት በቤተሰብ ጤና ፓኬጅ ክፍል መካተት ይኖርበታል። የጤና ጥበቃ ሚኒስቴርም ከትምህርት ሚኒስቴርና ከሴቶች፣ ሕፃናትና፣ ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር መሥራት ይኖርበታል። የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ከማህበረሰብ አቀፍ ጤና መልዕክተኞች ጋር በቤትና በጤና ኬላዎች ለሚከናወኑት ተግባራት ኃላፊነት አለባቸው። በወላጆች ትምህርት ከፅንስ እስከ 3+ዓመት ላለው ወቅት የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ የትምህርት ሚኒስቴርና የሴቶች ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የጋራ ኃላፊነት አለባቸው። ሌሎች የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ኃላፊነቶች የንጽህና፣ የምግብ ደህንነትና የጤና አጠባበቅ ትምህርት መስጠት ናቸው።

## 6.5 የሴቶች፣የሕፃናትና የወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር (ሴሕወጉሚ)

ይህ ሚኒስቴር በተለያዩ ባህሎች ውስጥ የሚገኙ ጠቃሚ የልጅ አስተዳደግ ዘዴዎችን መለየትና ማዳበር ከብዙዎቹ ኃላፊነቶቹ ውስጥ አንዱ ነው። ከዚህም ሌላ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በአጠቃላይ በሕፃናት ዕድገት ላይ ስለሚያስከትሉት አሉታዊ ተፅዕኖ በማስተማር ለማስወገድ ጥረት ያደርጋል። የሕፃናት መብት፣ ጥበቃና እንክብካቤ እንዲጎለብት ይሠራል። ስለ ሕፃናት መብቶችና ደህንነት ግንዛቤ ይፈጥራል። የተበደሉ ሕፃናት ጥበቃ፣ ድጋፍና፣ እንክበካቤ እንዲያገኙ ከሚመለከተው አካል ጋር

የመሥራት ኃላፊነት አለበት። ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሁሉም ሕፃናት ፆታን ወይም አካል ጉዳትን መሠረት ባላደረገ መልኩ ያለ መድሎ እኩል እንክብካቤ ማግኘታቸውን ያረጋግጣል። በአጠቃላይ የሕፃናት፣ የእናቶችና የሴቶች መብቶችን ማስጠበቅ፣ የቅስቀሳ ሥራ ማካሄድና ለሕፃናት የሚሰጡ አገልግሎቶችን ማገዝ ከወሳኝ ሚናዎቹ ውስጥ ጥቂቶቹ ናቸው። የሚኒስቴር መ/ቤቱ የተለያዩ የሴቶች ማህበራትን በማንቀሳቀስና በማስተባበር ማህበረሰቡ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ማዕከላት በማቋቋም እንዲሳተፍ በማነሳሳት በኩል ጠቃሚ ሚና ይጫወታል።

## 6.6 የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ለቀልዘእት በጀት መመደብና በሁሉም የልማት ዕቅድ ውስጥ በተለያዩ ደረጃዎች የቀልዘእት ፕሮግራምን ማካተት አለበት። የቀልዘእት ፕሮግራምን ለማገዝና ለሁሉም ተሳታፊ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች አስፈላጊውን ሀብት ለማግኘት አገር በቀልና ዓለም አቀፍ ድርጅቶችን በማንቀሳቀስ ሁኔታዎችን ያመቻቻል። የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በሀገራዊና ዓለምአቀፍ ለጋሽ ድርጅቶች መካከል አጋርነትን በመፍጠር ረገድ ጠንካራ ሚና ይጫወታል።

## 6.7 ዩኒቨርስቲዎችና የቀልዘእት የልህቀት ማዕከል

የቀልዘእት የልህቀት ማዕከላት በመጀመሪያ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ቀጥሎም በሌሎች ዩኒቨርስቲዎች፣ የመምህራን ትምህርት ተቋማትና ጤና ኮሌጆች መቋቋም አለባቸው። የቀልዘእት የልህቀት ማዕከላት የምርምርና የፈጠራ ሥራ ይሠራሉ፣ ባለሙያዎችን በዲግሪ ደረጃ በማሰልጠን ያዘጋጃሉ። በተጨማሪም የምርምር፣ የማማከርና የፈጠራ ሥራ ኃላፊነትን ይወስዳሉ።

## 6.8 የሃይማኖት ተቋማት(የእምነት ድርጅቶች)

እነዚህ ድርጅቶች ለሕፃናት የጤናና የትምህርት አገልግሎት ሰጪ በመሆንና ቀልዘእትን በመደገፍ ጠቃሚ ሚና ይጫወታሉ። በተጨማሪም የቀልዘእት ፕሮግራምን አቅም የማጎልበት፣ የማስተዋወቅና ሀብት የማንቀሳቀስ ሚና ይኖራቸዋል።

## 6.9 የሁለትዮሽና የብዙዮሽ የልማት አጋሮች

እነዚህ የልማት አጋሮች ሀብት በማንቀሳቀስ ለቀልዘእት እገዛ ያደርጋሉ። እንዲሁም የማስተዋወቅ ሥራና የቴክኒክ ድጋፍ በማድረግ የፖሊሲ ማዕቀፉን ተግባራዊነት ያግዛሉ። አቅምን የመገንባትና በአጋሮች መካከል ትስስርን በመፍጠርና በማጠናከር ረገድ ሚና ይኖራቸዋል።

## 7. ማጠቃለያ

ይህ የፖሊሲ ማዕቀፍ አጠቃላይና አዋጭ ለሆነ የቀልዘአት ዕድገት መሠረት ነው። የዚህ ፖሊሲ ትግበራ የኢትዮጵያ ሕፃናት ጤናማ የሕይወት ጅማሬ እንዲኖራቸው፣ ችሎታቸውን ማበልፀግና ማሳደግ የሚችሉበት አነቃቂ አካባቢ እንዲያገኙ፣ አምራችና ተንከባካቢ ዜጋ እንዲሆኑ ለማረጋገጥ የሚረዳ እና ወደፊት የሚያስኬድ እርምጃ ነው።

የነባራዊ ሁኔታ ትንተናው እንደሚያሳየው በሀገሪቱ የቀልዘአት አገልግሎት አለ ሊባል የማይቻልበት ደረጃ ላይ ነው። ስለዚህ ሕፃናት ጤናማ ሕይወት እንዲጀምሩ፣ በምቹ፣ ተንከባካቢና አነቃቂ አካባቢ እንዲያድጉና እምቅ ችሎታቸውን ሙሉ በሙሉ ማበልፀግ እንዲችሉ አስፈላጊውን መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስን ይጠይቃል።

በፖሊሲ ማዕቀፉ የቀልዘአት አገልግሎት አሰጣጥ በአራት ምሰሶዎች እንዲዋቀር ተደርጓል። እነዚህም፡-

ሀ. የወላጆች ትምህርት፣

ለ. የጤናና የቀዳሚ ማነቃቃት ኘሮግራም (ከቅድመ ወሊድ እስከ 3+ዓመት)፣

ሐ. የቅድመ መደበኛ ትምህርት (4-7 ዓመት)፣

መ. መደበኛ ባልሆነ መንገድ ለት/ቤት ዝግጁነት ኘሮግራም ናቸው።

የቀልዘአት ስኬት የሚወሰነው በሁሉም ደረጃ ባሉ የትምህርት፣ የጤናና የሴቶች፣ የሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ መሥሪያ ቤቶች መካከል በሚኖረው ትብብር መሆኑ ጥርጥር የለውም። ኘሮግራሙ በሰፊው በሀገር አቀፍ ደረጃ ከመተግበሩ በፊት የሙከራ ትግበራ መካሄድ አለበት። ስለሆነም በወላጆች ትምህርት፣ በጤናና ቀዳሚ ማነቃቃት ኘሮግራምና በማህበረሰብ አቀፍ መደበኛ ያልሆነ የት/ቤት ዝግጁነት የሙከራ ጥናት ይካሄድባቸዋል። በዚህ በኩል አቅምን ለማዳበር ከፍተኛ ጥረት መደረግ አለበት። ለእነዚህ ተግባራት የሚውል ሀብት ማግኘት ሌላው ቁልፍ ጉዳይ ነው።

አፈፃፀሙን በዕቅዱ መሠረት እውን ለማድረግ ከተለያዩ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችና ለጋሽ ድርጅቶች ተወካዮችን ያቀፈ ስልጣን ያለው ስቲሪንግ ኮሚቴ ይደራጃል። ይህ መሪ ቡድን የቀልዘአት ፖሊሲ ማዕቀፍን ትግበራ የማደራጀትና የመቆጣጠር ኃላፊነት ይኖረዋል። ስቲሪንግ ኮሚቴውም የትግበራው ዋና አንቀሳቃሽ የሆነው ግብረኃይል ከቀልዘአት ክፍል ጋር ተቀናጅቶ እንዲሰራ ያደርጋል።

የቀልዘአት የልህቀት ማዕከላት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ በሌሎች ዩኒቨርስቲዎች፣ በመምህራን ትምህርት ተቋሞችና ጤና ኮሌጆች ይቋቋማሉ። በክልልና ወረዳ ደረጃ የተለያዩ የመንግሥት ተቋማት ለቀልዘአት ፖሊሲ ማዕቀፍ ትግበራ የጋራ ኃላፊነት አለባቸው። በቀበሌ ደረጃ የሚቋቋመው የቀልዘአት ትግበራ ኮሚቴ በማህበረሰቡ ውስጥ ለሚካሄዱ ለሁሉም የቀልዘአት ተግባራት ከንውን ኃላፊነት አለበት።

በአጠቃላይ በአራቱም ምሰሶዎች የተዋቀረ ግልፅና ጠንካራ ማዕቀፍ ተቀምጧል። ይህም የፖሊሲ ማዕቀፉ ዓላማዎች እንዲሳኩና አዋጭና ውጤታማ በሆነ መልክ ይተገበሩ ዘንድ ይረዳል።

ከዚህ በታች ስትራቴጂያዊ ዓላማዎች ተዘርዝረዋል፤ እንዲሁም በእያንዳንዱ ዓላማ ሥር አራቱ ምሰሶዎች እንዴት የዓላማዎቹን ማሳካት እንደሚያረጋግጡ ቀርቧል።

ሀ. ለቀልዘአት ወጥነት ያለው አስተዳደራዊ መዋቅር ማዋቀርና ፕሮግራሙ በሁሉም ተዛማጅ ብሔራዊ ፖሊሲዎች መካተቱን ማረጋገጥ፤ የአስተዳደር መዋቅሩ ወጥነት የሚኖረው የአመራር ደረጃዎችና ተዛማጅ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች/ዘርፎችን ካጠቃለለ ነው። የአስተዳደር መዋቅሩና የአራቱ ምሰሶዎች አቀራረብ ቀልዘአትን በሁሉም ተዛማጅ ብሔራዊ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ለማካተት ምቹ ያደርገዋል።

ለ. ተደራሽ፣ ፍትሐዊና ጥራት ያለው የቀልዘአት አገልግሎት ለሁሉም ሕፃናት በተለይ ለችግር ተጋላጭ ለሆኑ፣ ልዩ ፍላጐት ላላቸውና ለተዘነጉ ሕፃናት ልዩ ትኩረት በመስጠት ማዳረስና ድጋፍ ማድረግ። አሁን ባለው መዋቅር የተገነባው የአራት ምሰሶዎች አቀራረብ የተለያዩ የቀልዘአት አገልግሎት አሠጣጥ ትግበራን ሊያረጋግጥ ይችላል። በወላጆች ትምህርት፣ ጤናና ቀዳሚ የማነቃቃት ፕሮግራም ሙከራና ማህበረሰብ አቀፍ የቅድመ መደበኛ ት/ቤቶችን በማቋቋምና በማሳደግ የተቀናጀ አገልግሎት ይሰጣል። መሠረታዊ አገልግሎት በመስጠት መደበኛ ባልሆኑ መንገዶች ፈጣንና ብዙ ወጪ በማያስወጣ አኳኋን ማዳረስ ይቻላል። በአራቱ ምሰሶዎች እንደተገለጸው ተጋላጭ ለሆኑ፣ ልዩ ፍላጐት ላላቸውና ለተዘነጉ ሕፃናት ልዩ ትኩረት ይሰጣል።

ሐ. ለጋ ሕፃናትን ከማንኛውም ዓይነት ጥቃትና ጎጂ ልምዶች እና ድርጊቶች መጠበቅ በአራቱ ምሰሶዎች በተለይ በወላጆች ትምህርት ውስጥ የሕፃናት መብቶችና ጥበቃ ቁልፍ ጉዳዮች ናቸው። የሴቶች የሕፃናትና የወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የሕፃናት መብቶችና ጥበቃን በተመለከተ የትግበራ ስትራቴጂ በማዘጋጀት የመሪነት ድርሻን ይወስዳል።

መ. በሁሉም ባለድርሻዎች መካከል አጋርነትንና ትብብርን ማጎልበትና ማጠናከር ለሕፃናት አገልግሎቶችና ፕሮግራሞች ውጤታማ አቀራረብ አስፈላጊ ነው። የአስተዳደር መዋቅሩ በሁሉም ባለድርሻዎች መካከል መተባበርን ያረጋግጣል። የልህቀት ማዕከልና በየመ/ቤቱ የሚቋቋመው የቀልዘአት ክፍል በዚህ ረገድ ጠቃሚና አጋዥ መሣሪያ ይሆናሉ። ብሔራዊና አለማቀፋዊ ግንኙነትንም ይፈጥራሉ።

ሠ. ከቅድመ ውልደት እስከ ሰባት ዓመት ላሉ ሁሉም ሕፃናት ጥራት ያለው አገልግሎትን ለማረጋገጥ አስፈላጊ ሀብትን ማንቀሳቀስ፣ ማቀድና መመደብ ያስፈልጋል። የስቲሪንግ ኮሚቴው ዋና ተግባር በስትራቴጂያዊ የአፈፃፀም እቅድ እንደተጠቀሰው የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ አስፈላጊውን መዋዕለ ንዋይ ማስገኘት ነው። ለጋሽ ድርጅቶች ለትግበራ፣ ለማሻሻል፣ አቅም ለመገንባትና ለሙከራ ገንዘብ ይሰጣሉ ተብሎ ይጠበቃል። ኮሚቴው ሁሉም ባለድርሻ አካላት መሳተፋቸውን ያረጋግጣል።

## አንዳንድ የእንግሊዝኛ ጽንሰ ሀሳብ ፍቺዎች

| | |
|---|---|
| **Accessibility** | ተደራሽነት |
| **Assessment** | ዳሰሳ/ፍተሻ |
| **Bilateral** | ሁለትዮሽ |
| **Caregiver** | ተንከባካቢ |
| **Child Survival** | የልጆች ሕልውና |
| **Child-to-Child** | ልጅ፣ለልጅ |
| **Corporal Punishment** | አካላዊ ቅጣት/ግርፋት |
| **Culturally Relevant** | ባህላዊ አግባብነት |
| **Development Partners** | የልማት አጋሮች |
| **Developmentally Appropriate** | የዕድገት ደረጃን ያገናዘበ |
| **Disadvantaged Children** | የተበደሉ ልጆች |
| **Early Childhood Care and Education** | የቀዳማይ ልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት |
| **Early Stimulation** | ቀዳሚ ማነቃቂያ |
| **Equity** | ፍትሐዊነት |
| **Center of excellence** | የልህቀት ማዕከል |
| **Forward** | መልዕክት |
| **Frameword** | ማዕቀፍ |
| **Holistic Development** | ሁለንተናዊ ዕድገት |
| **Identification** | መለያ |
| **Inclusion** | መካተት |
| **Inclusive Education** | አካቶ ትምህርት |
| **Interaction** | መስተጋብር |
| **Investment** | መዋዕለ ንዋይ |
| **Mainstream** | ማካተት |
| **Manual** | መመሪያ |
| **Monitoring** | ክትትል |
| **Multi Sectorial** | ብዝሀ ክፍል |

| | |
|---|---|
| **Multilateral** | ብዙዬሽ |
| **Pillars** | ምሰሶዎች |
| **Pilot Testing** | የሙከራ ጥናት |
| **Potential** | እምቅ ችሎታ |
| **Preface** | መቅድም |
| **Resource Mobilization** | ሀብት ማፈላለግ |
| **Safety Net** | ሴፍቲ ኔት |
| **Sector** | ክፍል |
| **Social Network** | ማህበራዊ መረብ |
| **Source** | ምንጭ |
| **Special Need** | ልዩ ፍላጐት |
| **Survey** | ጥናታዊ ዳሰሳ |
| **Survival Needs** | የሕልውና ፍላጐቶች |
| **Vulnerable Children** | ለችግር የተጋለጡ ሕፃናት |